ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

የቲዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

ሀምሌ 1961 ዓ. ም.

ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

የቲዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

አዘጋጅ፦ ነገደ ጎበዜ

የዝግጅት አማካሪ፦ ፍቅሬ መርድ

ሀምሌ 1961 ዓ. ም. ዋጋው 1 ብር

ይዘት | ገፅ

ርእሰ አንቀፅ 1

ላብ-አደሩና ጨንነት በኢትዮጵያ 10

የኢትዮጵያ ላብ-አደር ህዝብ ሁኔታ 30

ከቪየትናም ጦርነት ምን ትምህርት እናገኛለን 39

መቅድም፣

ለአንድ ሬቮሉሽናዊ ድርጅት ከሚያስፈልጉት ዋና ዋና መሳሪያዎች አንዱ መፅሄት ነው። እርግጥ ነው፤አድኃሪያዊ ድርጅቶችም በመፅሄት ይጠቀማሉ።ነገር ግን የአድኃሪያዊ መፅሄቶች ጥረት ድንቁርናንና ፍርሃትን . . . በህዝብ መካከል ለመዝራት፤የበዝባዦንና ያለን ስርአት ዘላለማዊ አስመስሎ ለማቅረብ ሲሆን የሬቮሉሽናዊያኑ ደግሞ እውቀትን፤ድፍረትንና ራስን ማወቅን ለህዝብ ለማስተማር፤የበዝባዥ ስርአት መገለበጥ እንደሚገባው ለማሳየት ነው።

በመፅሄቶች ጠቃሚ ትምህርትን ለማስፋፋት፤መሰረታዊ አሳቦችን ለማሰራጨት እንደሚቻል በትክክል በመገንዘብ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ለየደረሱበት የትግል ደረጃ መሪ አሳብ ማሰራጫ የሚያገለግሉ መፅሄቶችን ማውጣት ከጀመሩ ብርከት ያሉ አመታት አልፈዋል።

በመጀመሪያ ብርከት ያሉ ቅርንጫፍ ማህበራት የየራሳቸው መፅሄቶች ነበሯቸው።የተማሪዎች ትግል ከፍ እያለ መሄዱ የፖለቲካ ህሊናቸውን መዳበር ሲያስከትል የትግላቸውንም መቀናበር ጠየቀ። ለዚህ ነው በውስጥና በውጭ የሚገኙ ማህበሮቻችን በያሉበት ጠቅላይ ማህበሮቻቸውን ከፈጠሩ በኋላ የየራሳቸውን አዘጋጅ ቦርድ በማቋቋም በአውሮፓ ትግላችንንና ታጠቅን፤በሰሜን አሜሪካ "ቻሌንጅን"፤በኢትዮጵያ ታገልን በተቀናበረ መልክ ማውጣት የጀመሩት።

አሁን ባለንበት ወቅት የተማሪዎች የትግል ደረጃ ከፍ ያለ ለመሆኑ በቤትም ሆነ በውጭ የሚያከናውኗቸው ሬቮሉሽናዊ ድርጊቶች ትክክለኛ ማስረጃዎች ናቸው።የደረሱበትን ከፍተኛ ፖለቲካዊ ህሊና ለመረዳት የቀመጧቸውንና የተሰለፉባቸውን አላማዎች መመልከት ብቻ ይበቃል።አሁን መከተል የነበረበት እርምጃ ትግሉን በበለጠ ማቀናበር ነበር።

በዚህ ታሪካዊ ፍላጎት ተፀንሶ የተወለደው አለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እንደዋና ተግባር አድርጎ የወሰደው የስራ ፕሮግራም በያለበት የሚካሄደውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ትግል ማቀናበር ነው።የአለም አቀፍ ጊዜያዊ ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ባደረጋቸው ሁለት ስብሰባዎች ላይ ዝርዝር

የስራ ፕሮግራም እያወጣ ለአባል ማህበራት አስተላልፎአል፤ስራቸውን ሊያከናውኑ የሚችሉበትን ዘዴ አንድ ባንድ ጠቅሶ አመልክቶአል።በዚህ አመት ሊዬዥ ውስጥ ከ"ኦገስት" 7 – 10.69 ባደረገው ስብሰባ ላይ ከተነጋገረባቸው ጉዳዮች አንዱ "የመፅሄት ማቀናበር" ዘዴ ነበር።

ከፍ ብለን እንደተናገርነው ሁሉ በየአገሩ(ኢትዮጵያ፤አሜሪካ፤ አውሮፓ)የሚገኙት አባል ማህበራት የየራሳቸው መፅሄቶች አሏቸው።አሁን የተደረሰበት የትግል ደረጃ ግን መፅሄቶቻችን በይዘታቸውም ሆነ ባስተታተማቸው በበለጠ ዘዴ እንዲቀናበሩ ይጠይቃል።ይህንን በመረዳት፤ላይ በተጠቀሱት ቀናት በሊዬዥ የተሰበሰበው የአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ጊዜያዊ ኮሚቴ፤በጉዳዩ በሰፊው ሀሳብ ለሀሳብ ከተለዋወጠ በኋላ፤በዚህ አመት ጀምር መፅሄቶቻችን በአለም አቀፍ ማህበር አቀናባሪነት እንዲዘጋጁ ወሰነ።መፅሄቶቻችንም ‹አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መፅሄት› በሚል ስም እንዲታወቁ ውሳኔ ... አባል ማህበራት ውሳኔውን አባል ማህበራት በሙሉ ተቀብለውታል።

ርእሰ አንቀፅ

ፀረ–ባላባት ፀረ–ኢምፔሪያሊስት

የዛሬው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ፀረ–ባላባትና ፀረ–ኢምፔሪያሊስት መሆኑን ደጋግመን ገልፀናል።ፀረ-ባላባት ነን፤ምክንያቱም በባላባቶች ፈላጭ ቆራጭነት ላይ የተመሰረተው ስርአተ ማህበራችን‹በስብሷል›እንላለን።ይህም ማለት ከእንግዲህ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማንኛውም አይነት መሻሻል የሚገኘው ስርአቱን ለመጠጋገን በከንቱ መሞከር ሳይሆን ይህ ስርአት ፈርሶ አዲስ፤ለወቅቱ፤ለሀገራችን፤ለህዝባችን የተስማማ (ማለት ለእርምጃው ረዳት እንጅ እንቅፋት የማይሆን) ስርአተ–ማህበር ስናቆም ብቻ ነው።ችግሩ ይህ ስርአት እኛ ስለጠላነው፤የህዝብ እድገት እንቅፋት ስለሆነ፤ገፊኛ ስርአት ስለሆነ ብቻ በገዛ ራሱ ተንኮትኩቶ አይወድቅም።ስርአቱ ጥቅማቸውን የሚያዳብርላቸውና እሱ እስካለ ድረስ ብቻ መቆም የሚችሉ ሀይሎች እየጠጋገኑ እድሜ ሊሰጡት ይፈልጋሉ፤ስርአቱን ለመሻር እነሱን ታግሎ መጣል ያስፈልጋል።ይህንንም ትግል በየጠቅላይ ግዛቱ፤በየአውራጃው በየወረዳው፤በጭሩ የባላባት ጭቆና በሚገኝበት በየሸርኩቻው ሳይቀር እየገፉ መምራት ያስፈልጋል።ከዚህም እማምረን ፀረ–ኢምፔሪያሊስት የሆነ ትግል መምራት አለብን። ለምን? ምክንያቱም ዛሬ ኢምፔሪያሊስቶች አዲስ ከውጭ መጥተው የተደረቡና ህዝቡን በይበልጥ ያራቆቱት ዘራፊዎች ብቻ አይደሉም። የምንቶቹም ዘራፊዎች የባላባቶቹ ዋና ጠባቂዎች እነሱው ናቸው። ከዚህም በላይ ደግሞ የባላባቶች አቋም ነገ ተሸንፎ ቢወድቅም ኢምፔሪያሊስቶች አብረውት ካልተደመሰሱ ጥቅማቸውን ለመጠበቅ፤የጀመሩትን ብዝበዛ ለመቀጠልና ለማጠንከር እነሱው በፈጠሩት ቡርዧዊ አማካይነት መልክ ለውጠው ለመምጣት ስለማይመለሱ ነው።የባላባቱን አገዛዝ በትግላቸው ጥለው ‹እፎይ ነፃ ወጣን ሲሉ› ኢምፔሪያሊስቶች በሀገሩ ቡርዧዊ አማካይነት ገብተውባቸው ትግላቸው ከንቱ ሆኖ ያገኙት ስንት ህዝቦች ናቸው? ከታሪክ መማር አለብን፤ሌሎች ያደረጉትን ስህተት መድገም የለብንም።ስለዚህ ትግላችንን ልንለያየው አንችልም። ነፃ ህዝብና ተራማጅ ኢትዮጵያ ከፈለገን ትግላችን ፀረ–ባላባትና

ፀረ–ኢምፔሪያሊስት መሆን አለበት።

እዚህ ላይ እንግዲህ አንዳንድ ጥያቄዎች መብራራት አለባቸው። የባላባት ስርአተ ማህበርና ኢምፔሪያሊዝም የህዝብ እድገት እንቅፋት የሆኑት ለምንድነው? ፀረ–ባላባትና ፀረ–ኢምፔሪያሊስት ነን የምንል ኢትዮጵያዊያን እንዴት፣ ከማንስ ጋር ሆነን ልንታገላቸው ይገባናል? ትግላችንንስ የምንመራው ወዴት ለመድረስ ነው? እነዚህ ሶስት ጥያቄዎች ሰፋ ያለ መልስ ያስፈልጋቸዋል፤ስለዚህ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የመጀመሪያውን ጥያቄ ለመተንተን ሞክረን የቀሩትንም ደግሞ ወደፊት ለማብራራት እንሞክራለን።

የዛሬው ስርአተ ማህበራችን የህዝብ እድገት እንቅፋት ነው ስንል እንቅፋትነቱ የት ላይ ነው? ታሪክን ዘወር ብለን ብንመለከት የባላባቶች አገዛዝ እንቅፋት መሆን የጀመረው ከህያንነቱ አንስቶ እንደሆን እናያለን።ደጋግመን እንደገለፅነው የዛሬ መቶ አመት የነበረው የባላባት ስርአትና የዛሬው የባላባት ስርአት አንድ መልክ የለውም።' ጥንት በሀገራችን ገበሬውና ባላባቱ ቅርብ ለቅርብ ይኖሩ ስለነበር ገበሬው እህሉን እየሚነሰት፤አጥሩንና ጉተራውን እየሰራለት፤ ሳር እያጨደለትና ቤቱን እየከፈከፈለት አንዳንዴም ከብቱን እያረባለትና እየጠበቀለት ይኖር ነበር። ባላባቱ የመሬቱ ባለቤት ከመሆኑም በላይ የቀበሌው ወይም የወረዳው አስተዳዳሪና ዳኛም ነበር።ሌባና ቀማኛ ያስይዛል፤ ያስፈርዳል፤ያገሩን ፀጥታ ባሽከሮቹና በወታደሮቹ ያስጠብቃል።ገበሬው በበኩሉ ካልገደለ፤ካልሰረቀ፤ ወይም ትልቅ ወንጀል ካልፈፀመ ከትውልድ ወደ ትውልድ በያዘው መሬት ላይ የመነቀል ስጋት ሳይኖርበት ይኖራል።(1) ስለዚህ እንደዛሬው ከመበስበሱ በፊት የባላባቱም ስርአት ገረኛም ቢሆን ዘራፊም ቢሆን በመጠኑ ጥቅምና አገልግሎትም ይሰጥ ነበር ማለት ነው። ዛሬ አቋሙ «በስብሷል» የምንለው ዝቅ ብለን እንደምናየው ከስርአተ ማህበሩ ማደግና ከታሪክ እርምጃ የተነሳ መሬቱ በታላላቅ ባላባቶች በመሰብሰቡና እነዚህ እፍኝ የማይሞሉት ታላላቅ ባላባቶች እንደቀድሞው ለህብረተ ሰቡ እርምጃ አስፈላጊ መሆናቸው ቀርቶ እንዲያውም እንቅፋት ስለሆኑት ነው።

(1) «ትግላችን» ልዩ ቱፐር ሚያዚያ 1961 ገፅ 3

በኢትዮጵያ የባላባት አገዛዝ ከተመሰረተበት አንስቶ እስከ ዘመነ መሳፍንት የማህበር ኑሮ መዳበርን እንዳስከተለ አይጠረጠርም።ከዘመነ መሳፍንት ንጥልጥል የባላባት ግዛት በኋላ የዛሬው የተባበረ የባላባት ግዛት ከቴዎድሮስ ጀምሮ እያደገ ሲመጣ ለህብረተሰቡ ወደፊት እርምጃ ነበር።ቴዎድሮስን "ተራማጅ" የምንለው ተበታትና ለንግድ፣ለግብርና ለፀጥታ አልመች ያለውን የመሳፍንት ሬውዳል አቋም በአንድነት አጠቃልሎ ህብረተሰቡን ወደፊት ለማራመድ በመሞከሩ ነው።ቴዎድሮስ በተለመው መንገድ ተከትሎ የኢትዮጵያን የተነጣጠሉ ሬውዳል ግዛቶች አጠቃልሎ ከጊዜው ፍላጐቶች ጋር ማስማማት በሚቀጥሉት ነገስታት ትከሻ ላይወደቀ።እንዲህ አይነቱ ማጠቃለል ለንግድ፣ለግብርና ለፀጥታ የተመቸ በመሆኑ አንድ አይነት እርምጃ ነበር።በዚህ አስተሳሰብ የኋድን እንደሆነ በሀገራችን ሬውዳሊዝም እያደገ አሁን እስከበሰበሰበት ድረስ ባለው ታሪክ ውስጥ ንጉስ ተፈሪንና አፄ ሀይለ ስላሴን በአንድ አይን እንመለከታቸውም።

የዛሬ አምሳ አመት በቴዎድሮስ የተጀመረው ባላባቶችን በአንድ ግዛት ስር አድርጐ መሰብሰብ ገና ያላለቀ ተግባር ነበር።ንጉስ ተፈሪ፤የጊዜው ተራማጅ ሀይሎች ግንባር ቀደም፤(የኢያሱን መውደቅ ወደ ጐን ብንተወው) ሀገሪቱን ወደ ታባ[illegible]ን የባላባት ስርአት ወደ ኋላ ለመመለስና የታሪክን እርምጃ ለመግታት የሚጣጣሩትን አድሀሪ ባላባቶች በመቋቋም አገሪቱን በእጁ ስር ለመሰብሰብ በቃ።ከዚያም የሚያድገው የባላባት ስአርት በሚጠይቀውና በሚችለው ልክ ሀገሪቱን ወደፊት ለመምራት ለዛሬው ትውልድ የማያስደንቁንን፤በጊዜው ግን ለሀገሪቱ ፍፁም አዲስና ታይተው የማይታወቁ ታላላቅ እርምጃዎች ወስዷል።አቋሙ እንዲያድግ ጊዜው የሚጠይቀውን ፀሀፊዎች ለማፍራት ትምህርት ቤት ሲከፈት፤ጊዜው የሚጠይቀው የአስተዳደር ዘዴ ስራ ላይ ሲውል፤ኢትዮጵያ በአለም ማህበር ጉባታ ስትከፈል ...ወዘተ. ይህ ሁሉ ለጊዜው ግንባር ቀደም የሆነ አስተያየት የሚያስገኘው እርምጃ መሆኑ አይካድም።ንጉስ ተፈሪ ይመራው የነበረው ስርአተ ማህበር ገና አልበሰበሰም ነበር፤ምክንያቱም ራሱ ለማደግ ህዝቡንም በመጠኑ ወደፊት ለማራመድ ይገደድ ነበር።ዛሬ አፄ ሀይለ ስላሴ የሚመራው ስርአ

ተ ማህበር «በስብሷል» የምንለው ከእንግዲህ ለማደግ ስለማይችልና ጥቅሙንም ለማዳበር ህዝቡን ወደፊት በማራመድ ሳይሆን፣ይበልጥ በመጨቆን፣ይበልጥ በመዝረፍ፣ይበልጥ መብቱን በመገፈፍ ብቻ ስለሆነ ነው። ለዚህ በቅርቡ በጉጃም ጠቅላይ ግዛት የግብር ጉዳይ ያመጣውን «አለመግባባትና» ደግሞ ሰሞኑን የወረደብንን ፋሽስታዊ«ይዞ የማሰር ህግ» መጥቀስ ብቻ ይበቃል። ሌላ ምሳሌ ለመስጠት የዛሬ ሃምሳ አመት ማደግ የሚፈልገው የባላባቶች ስርአተ ማህበር ወጣቶችን "ተማርልኝ" እያለ በግድ እያፈሰ ወደ ትምህርት ቤት ይወስዳቸው እንደነበር ተደጋግሞ ተነግሮናል። ዛሬ ማደግ የማይችለው የባላባቶች ስርአት ለመቆም የሚችለው ተራምዶ ሊያልፈው የተንቀሳቀሰውን ህዝብ በመግታት ብቻ ሲሆን እናያለን። ወጣቶች ዛሬም ከመንገድ ይታፈሳሉ፣ግን የሚወሰዱት ወደ ወህኒ ቤት ነው። ዛሬ ጠቡ ህዝቡ ብርሃን ልይ ሲል ስርአቱ ደግሞ "አትማሩብኝም" እያለ በመፍጨርጨሩ ነው።

ባጭሩ ዛሬ ህዝቡ ጭቆናው ተደራርቦበት ልራመድ፣ልገስግስ፣ይለፍልኝ እያለ ወደፊት ለመንጠራራት ሲተናነቅ ይታያል። "መሪዎቹ" ደግሞ የታሪክ እርምጃ ሳያውቁት ጥሏቸው ስለሄደ ከኋላ ቀርተው እንዳይራመድ፣እንዳይገሰግስ፣እንዳያልፍለት አውተውትበው ሲጎትቱት ይታያሉ። በህዝቡ ታልፈው ሄደዋልና የወደፊት እርምጃ የሚጠይቀውን ፖለቲካ ለመከታተል በፍፁም አይችሉም። የባላባታዊው ስርአተ ማህበር ህዝቡን መምራት ካቆመ ዘመን አልፎታል። ከእንግዲህ መከራው አልፎት የሄደውን ህዝብ ወደኋላ ለመጎተትና እንደተመቸው ለመንዳት ነው። ታዲያ ይኸ ደግሞ ችግር ነው። አንድ ህዝብ ይመራ እንደሆን እንጂ እንደከብት አይነዳም።

ለማጠቃለል ያህል፣በሚያድገው የባላባቶች ስርአተ ማህበር ውስጥ ባላባቶች፣በመጠኑም ቢሆን፣በስርአቱ ውስጥ የተወሰነና በሚገባ የሚያከናውኑት አስፈላጊ የሆነ ተግባር ነበራቸው። ስለዚህ እርምጃን ይረዱ እንደሆን እንጂ አያደናቅፉም ነበር። ዛሬ ግን ስርአቱ በስብሷል፣መፍረስ አለበት የምንለው ታላላቆቹ ባላባቶች (1) እንደቀድሞው ተፈላጊነት ስለሌላቸው፣(2) አልፈው ተርፈው የእድገታችን እንቅፋት ስለሆኑ ነው። ነገሩን በይበልጥ እንተንትነው፣ዛሬ እኛ እናስፈልጋቸዋለን እን

ጂ እነሱ አያስፈልጉንም። የዛሬ መቶ አመት ጣሊያን በዚህ መጣ ሲባል ሰዎቻቸውን ሰብስበው ተንደርድረው የሚጋጠሙት እነራስ አሉላ ነበሩ። ዛሬ ጠላት በዚህ መጣ ቢባል ራስ ደጃዝማቾቻችን በየት በኩል እንደሚንደረደሩ እናውቀዋለን፣አይተንቀልም። የዛሬ ራሶች ሰዎቻቸውን ሰብስበው ተንደርድረው ሲገጥሙትና ሲራኮቱ በህልማችንም አይመጡብን።

ታማኝነቱ አይባሉ አዲስ አበባ የተቀመጡት ታላላቅ ባላባቶችና ድሀውን ህዝብ ከወሎ፣ከትግሬ፣ከቤገምድር ...ወዘተ. ወደነሱ የሚያንጓጉት ለማንከራተትና ወግ የሌለው ሞት ቀባሬ ለማሳጣት እንጅ ፍርድ ለመስጠት እንዳልሆነ በግልፅ አይተናል። የእውቀት ብርሀን ምንጭ አይባሉ ዛሬ ስርአታቸውን ቀጥ አድርጎ የያዙላቸው ቢሮክራት፣ እነሱው ደጋግመው እንደሚያስታውሱን «ከማንም ልጅ የተውጣጣ» ነው። የንፁህ ባህል ምንጭ አይባሉ መሰልጠን ፈረንጅ መሆን መስሏቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን ረስተዋል፣ህዝባቸውን ንቀውታል፣ተጠይፈውታል። ባጭሩ ታላላቆቹ ባላባቶች ለሀገሪቱ እርምጃ ምንም አይነት ተፈላጊነት የላቸውም።

የባሰ አለ። አልፈው ተርፈው ለህዝቡ እርምጃ እንቅፋት ሆነውታል። ሌላውን ሁሉ እንተወውና በኢኮኖሚ በኩል ያለውን ችግር እንይ። ግልፅ ነው፣አንድ ህዝብ እንዲራመድ ምርቱን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን መጠነኛ ኑሮውን ለማሸነፍ ከሚያስፈልገው ተርፎ የሚቀረውን ሀብት እንደገና ስራ ላይ እያዋለው ኑሮውን ይበልጥ የተመቻቸ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ድርጅቶች ማቋቋምና ምርቱንም ይበልጥ ለማሳደግ የሚያስችሉትን የስራ ዘዴዎች ማስፋፋት አለበት። ከዚህ ሌላ ቢወድቁ ቢነሱ ምንም አይነት የእርምጃ መንገድ የለም። ዛሬ በበሰበሰው የባላባታዊ አገዛዝ ስርአት ግን ምን እናያለን? የገበሬውን የላብ ፍሬ እያግበሰበሱ ስለሚወስዱት ገበሬው ምርቱን እንዳያሳድግ ያደርጉታል። ከዚህም ከሚያፈራው ሀብት እንዳይቆጥብ እንዳይሸር አድርጋ በኑሮ ጠርዝ ላይ ከምታንጠለጥለው ጉርሻው በስተቀር ምንም አይደርሰውም። አብዛኛው የላብ አደር የስራ ፍሬ እድገት እንደሚጠይቀው ተመልሶ እንዳይሰራበት፣ለጥቂቶች ምቾት ይረጫል። በዚህ ላይ ዝቅ ብለን እንደም

ናየው ላብ አደሩ የኢምፔሪያሊስቶች ዘረፋ ተጨምሮበታል።

ባላባቶች እራሳቸው ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር ተገጠሙ ወዲህ ዘረፋቸው ልክ እያጣ መሄዱን ማንም የሚያውቀው ነው። ምክንያቱስ? የድሮ ባላባት ከገበሬው የስራ ፍሬ ቢወስድ፣ መጠነኛ ኑሮውን ለማሸነፍ እንጅ እንደዛሬው ከህዝብ አንጀት የተጨመቀውን ሀብት ቅጥ ባጣ መንገድ ለመበተን አልነበረም።ያለውም ገበያና ፍላጐት የተወሰነ ስለነበር ዘረፋውም የተወሰነ ነበር።በዚህ ላይ ገበሬውና ባላባቱ በዚያችው በመንደራቸው አስም ውስጥ በመጠኑ ደስታንና መከራን አብረው የሚካፈሉ በመሆናቸው ድርቅ ሲሆን ያዝንለታል።ሲትረፈረፍ ግብር ያበላዋል፤በመጠኑ ይተዋወቃሉ፤በመጠኑ ይተዛዘናሉ፤ሲያስፈልግ ደግሞ ይረዳዳሉ።

የዛሬው ልዩ ነው።መጀመሪያ ታላቁ ባላባት ከመኖሩ በስተቀር ባስተሳሰቡ፤በባህሉ፤በኑሮ ዘዴው... የባህር ማዶ ሰው ሆኗል።አለበታው ሆን እንጅ ይህ የባላባቶችና የህዝቡ መራራቅ ብዙ የሚያዕረን ነበር።ነገሩን ለማንሳት ያህል፤ከኢምፔሪያሊስቶች በመገጠማቸው ብቻ «ፈረንጅ አምላኩ»ሆነው ህሊናቸው ተከላኽቶ ያለምእራባዊያን ስልጣኔ ሌላ የለሴ የሚመስላቸው ስንቱ ናቸው? ህዝባችንን የማይጠየፍ፤ባህላችንን የማይንቅ፤ከአዲሱ የባላባት ትውልድ ውስጥ እስከ ቋንቋችን ተጠይፎ አማርኛ የማይናገር ስንቱ ነው? ስንቱ ማንነቱን የረሳ«ኢትዮጵያዊ» አለ? ይህ ብቻ ሌላ ነገር ነው፤ወደፊት በሰፊው እንመጣበታለን። አሁን ወደዘረፋው እንመለስ።

በዝባዦቹ ባላባቶች ገበሬውን እያውቁትም።ችግሩም ሊገባቸው አይችልም።የመንደሯ አከባቢ፤የቀበሌዋ አለም ተሰባብራ ወድቃለች።ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ዛሬ ያለልክ የሚዘርፈውን ያህል፤ያለልክ ይንደላቀቃል።ሀብቱ ይገኝ እንጅ ዛሬ ገንዘብ የማይገዛው ምን አለ? ሀብቱ ይገኝ እንጅ ስንት ቪላ ይሰራል? ሀብቱ ይገኝ እንጅ አንዱ መኳንንት ብቻ በጀት ተሳፍሮ ገስገሶ ፓሪስ ውሎ ቢያድር ስንት ሽህ ብር ሊወጣ ይችላል?ደግሞስ የአገሩ ባንክ ከሌታመነ ውጭ አገር ባንክ ለሚሸሸው የህዝብ ሀብት ምን ወሰን ሊኖረው ይችላል?ግልፅ ነው፤የባላቱ ዘረፋ ልክ እያጣ መሄዱ።

በዚህ ላይ ደግሞ ኢምፔሪያሊስቶች የበኩላቸውን በቀጥታ ይዘርፋሉ።በፍጥነት ብዙ ትርፍ በሚገኝበት ቦታ እየገቡ የቻሉትን ያህል አገሪቱን ለማለብ ይሞክራሉ።አገራቸዉ ላላቸው እንዱስትሪ ጥሬ እቃ የሚገዛው ከተበዝባዥ አገር ነው።የፋብሪካ እቃዎችም ወደዚሁ ወደ ተበዝባዥ አለም የሚፈሰው ህዝቡን ከችግሩ ለማላቀቅ ሳይሆን፤በነዚህ የምቾት እቃዎች ጨቋኞቹን እያስጐመጁ በህዝቡ ላይ ያለውን ዘረፋ ለማጠንከር ነው።በዚህ ላይ ደግሞ የተዛባ ግኛቸው አለ።በየስታቲስቲኩ እንደምናየው ለገዢዎቻችን አንዲት መኪና ለማስመጣት የዛሬ ሰላሳ አመት ሃያ ጆንያ ቡና ያስፈልግ ነበር።ዛሬ ለአንዲት መኪና ሁለት መቶ ጆንያ ቡና አይበቃም።እንግዲህ ድሀው የሚያመርተው ባይጨምርም ባላባቶቹን በምቾት ለመጠበቅ በይበልጥ መበዝበዝ አለበት ማለት ነው።

ኢምፔሪያሊስቶች ይህ የተዛባ ንግድ ጠቅሟቸዋልና «እንቀጥላለን» ይሉናል ኢኮኖሚስቶቻቸው ለእንዲህ አይነቱ ዘረፋ ቲዎሪ አውጥተዋል፤‹ኮምፓራቲቭ ኮስት ቲዎሪ»ይሉታል።አስተሳሰቡ እንዲህ ነው፡—«እናንተ ቡና ማፍራት ይቀናችኋልና እንዲያው ሌላውን ሁሉ ትታችሁ ቡናችሁን ዝሩ፤እኛ የኢንዱስትሪን ስር ተክነንበታልና ሌላውን ሁሉ ትተን፤አስፈላጊም ነውና፤ብረቱን፤አልሙዙን፤ማእድኑን ከናንተ እየገዛን እንዱስትሪያችንን እናስፋፋ።ሁላችንም በያለንበት ከልብ እንስራ፤ያመረትነውን ይዘን ኢንተርናሽናል ገበያ እንገናኝ» ይሉናል።

ግን ብዙ ችግር አለ።መጀመሪያ ሁላችንም በያለንበት በደንብ ብናመርት ኢንተርናሽናል ገበያ ለመድረስ እኛ ብዙ ችግር አለብን። ቡናችን ስዊዝ ከናል ሲዘጋበት አሁን እንደምናየው አፍሪቃን ዞሮ አውሮፓ ሳይደርስ መንገድ ላይ በስብሶ ይቀራል። የነሱ የብረት ስራ ነውና ጨረቃ ደርሶ በደህና ይመለሳል።በዚህ ላይ ኢምፔሪያሊስቶች ‹ቡና ይቀናችኋልና አምርቱ» የሚሉት እኛን ብቻ አይደለም፤በየደረሱበት ነው። ስለዚህ ቡና (ማንኛውም ጥሬ እቃ) ተግበስብሶ ወደ ኢምፔሪያሊስቶቹ ገበያ ሲደርስ ዋጋቸውን ያወርዱታል። ከዚህ በላይ የነሱን ኢኮኖሚ ጉንፋን የያዘው ቀን እኛን ተስቦ ይገለናል።እሺ ከሌናቸው ጣጣው ብዙ ነው።ዝም ከልን አገራችን ራሱን የቻለ ብሄራዊ ኢኮኖሚ መመስረቷን

ትታ ዘለአለማችንን የነሱው ዑና አቅራቢ ሆነን መቅረታችን ነው።እር
ግጥ ነው፤ዑና ቸርችር የተገኘ ሃብት ባላባቶቻችንን ለጊዜው ሊያገዳላ
ቅታቸው ይችል ይሆናል።ግን እውነቱን ያየነው እንደሁ ኢምፔሪያሊ
ስቶች የሚያቀርቡልን «ቲወሪ» በጭራሽ መሰረተ ቢስ ሆና እናገኘዋለ
ን።እርግጥ ኢምፔሪያሊስቶች እንደኛ ዑና ማምረት አይችሉም ይሆና
ል፤እኛ ግን እንደነሱ እንዱስትሪ ማቋቋም በፍፁም አይቸግረንም።ግ
እድትነብረቱ፤ናሱ፤ወርቁ፤አልማዙ እንደሆነ የሚጋዘው ከአፍሪቃ፤ከእስ
ያና ከላቲን አሜሪካ ነው።ስለዚህ ዑና አቅራቢ ሆነን የምንቀርበት ምክ
ንያት በፍፁም አይታየንም።ግን ብሄራዊ ኢኮኖሚያችንን ለመገንባት
ና ለማዳበር እንድንችል አስቀድመን ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል በመ
ምራት ብሄራዊ ነፃነታችንን ማግኘት አለብን።ያለዚያ እንደዚሁ ጥሬ ሸ
ቀጥ አቅራቢዎችና ድሆች፤ደንቆሮዎችና በሽተኞች ሆነን መግቀታችን
መቀጠሉ አይቀርም።እነሱ ደግሞ ከኛው በሚዘርፉት ሀብት እንዱስትሪ
ያቸውን እያስፋፉ፤እየበለፀጉ፤በእውቀት እየተትረፈረፉ መሬት ለቀው
ይሄዳሉ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የዛሬው ስርአተ ማህበራችን በሚገፉ
ውና በሚበትነው የህዝብ ሀብት የእድገት እንቅፋት መሆኑን በመጠኑ
ያስረዳን ይመስለናል።ታዲያ እንደዚህ ግፈኛና ታሪክ ያለፈበት ስርአ
[illegible] ቆሞ ለመሄድ ቻለ? ቆሞ መሄዱ እፍኝ ለማይሞሉ ታላላቅ
ባላባቶች የተመቸ ስርአት በመሆኑ ብቻ ነው።ምክንያቱም ይህ ሁሉ ሲ
ሆን ህዝብ አልተራመደም እንጂ ለነሱ ምንም የጉደለባቸው ነገር የለ
ም።እንዲያውም ለነሱ ሀገራችን ሰላምና፤ተራምዳ አብቃታለች።ተመች
ቷቸዋልና ከእንግዲህ በሀገሪቱ የሚሰራ ነገር የለም።የፊውዳሉ ኢኮኖ
ሚ ከዚህ በላይ ለማደግ ስለማይችል ዛሬ ፀሀፊውና መሀንዲሱ፤ሀኪሙ
ና ዘመናዊ እርሻ አዋቂው፤በጠቅላላ የተማረው ስራ ፈትቶ ቢንቀዋለል
ለነሱ ደንታ የላቸውም።ሀኪም ቤታቸው እንደሆነ አውሮፓ ነው፤መሀ
ንዲሳቸው እስከናዝሬት አስፋልት አንጥፏል፤የዘመናዊ እርሻ አዋቂው
እንደሁ አያስፈልጋቸውም፤ለእነሱ መንደላቀቂያ ያህል 23 ሚልዮን ኢ
ትዮጵያዊ ወሞፈርና በቀንበር አርሶ የሚያቀርብላቸው ይበቃቸዋል።እን
ዲህ ሆና ነው እንጂ ሀገራችን ገና ስንት መራመድ፤ስንት መሻሻል፤ስን

ት የስራ ውዝፍ አለባት!የተፈጥሮ ሀብቷ ሁሉ በሚገባ ተቀናብሮ ለህ
ዝቧ ጥቅም እንዲውል ልጆችዋ በሙሉ(ወጣት፤ሽማግሌ፤ወንድ፤ሴት፤የ
ተማረ፤ያልተማረ ሳይባል) ባንድነት ታጥቀን ሊተተቀን መስራት ሲገባ
ን አዲስ አበባ ብቻ ስንት ሽህ ወጣቶች «ስራ እያጡ» ይንቀዋለላሉ?

በዚህ አኳያ ስር ህዝብ መራመድ ከታተው እንግዲህ ምን
ማድረግ ይሻላል?ገበሬዎቻችን ህዝቡ ሽህ ጊዜ ይደንቁር እንጂ፤ይደህይ
እንጂ፤በበሽታ ይሰቃይ እንጂ ከትውልድ ትውልድ ሲያያዝ የመጣው ስ
ርአታችን አይፈርስብንም፤አይነካብንም ይላሉ።ስርአቱ ለጊዜው እንደ
ሚስማማ ተለውጦ ህዝብ ከሚፍታታና ወደፊት ከሚራመድ ያለው ስ
ርአት ተከብሮ «የሶስት ሽህ ዘመናት ታሪካችን» ባይፋለስ ይመርጣሉ።
እርምጃን የከለከለ፤ብርሃንን ያፈነ ስርአተ ማህበር እፍኝ ለማይሞሉ ዘ
ራፊዎች በመመቸቱ ብቻ እንደዚህ የሙጥኝ ብለው ስለያዙ ነው «እድ
ሃራ» የምንላቸው።የኛ አኳያ ደግሞ የተለየ ነው።ህዝብ ብርሀን ይይ እ
ንጂ፤ድንቁርና፤በሽታና ድህነት ከሀገራችን ገፅ ይጥፉ እንጂ የበሰበሰው
የባላባት ስርአት አያስረንም እንላለን።ስርአተ ማህበሩ ለህዝብ እድገት
እንቅፋት ከሆነ መፍረስ አለበት እንላለን።ይህ ነው የዛሬውን የኢትዮጵ
ያ ተማሪዎች ንቅናቄ «ተራማጅ» የሚያሰኘው።

የባላባቱ ስርአተ ማህበር ከኢምፔሪያሊዝም ገጥሞ መላው
ን የኢትዮጵያ ህዝብ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በሚሄድ ዘረፋ ወጥሮ
ይዞታል።ይህ እፍኝ ለማይሞሉ ዘራፊዎች ስለተመቸ ብቻ በአንድ ህዝ
ብ ላይ የተጫነ ቀንበር መውደቅ አለበት።ከፍ ብለን እንዳልነው በመረረ
ትግል እንጅ እኛ ስለጠላነው ወይም ግፈኛ አኳያ በመሆኑ ብቻ «እፍ»
ቢሉት ተንኮትኩቶ አይወድቅም።ስለዚህ በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊ
ዝም መቃብር ላይ የሁላችን የሆነች ህዝባዊት ኢትዮጵያን ለመመስረ
ት ኢትዮጵያዊያን የሆንን ሁሉ፤እፍኝ ከማይሞሉት ጨቋኞችና ደጋፊ
ዎቻቸው በቀር፤በአንድ የትግል ግንባር ውስጥ ተሰብስበንና ተደራጅተ
ን በአንድነት መራመድ አለብን።

ወዝ አደሩና ጤንነት በኢትዮጵያ

ከተስፋዬ ስዩም

ለሰው ልጅ ጥረትና ትግሉ መሰረት ከሆኑት አንደኛው ጤንነት ነው።ጤና ያለው ሰው ሊሰራ ይችላል፤በህይወቱም ደስታ ያገኛል። በኢትዮጵያ የወደፊት ተራማጅ ሀይሎች ሁሉ–በተለይ የተማሪ ማህበረሰብ–በየስብሰባዎቻቸው ላይ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች፤በሚወስዱዋቸው ውሳኔዎችና በሚተልሙዋቸው እቅዶች ለጤንነት ተገቢ ቦታውን ይሰጡታል።የኢትዮጵያ ተማሪዎች በየጊዜው በሚያደርጉት ውይይትና ትግል ውስጥ የአገራችንን የጤንነት ደረጃ ማሳደግ ከዋናው እቅዳቸው አንዱ ነው።ለዚህም በየጊዜው በሚያደርጉት ስብሰባ የሚያሳልፏቸውን ውሳኔዎች መመልከት ይበቃል።

በሚቀጥሉት ገፆች ስለ ኢትዮጵያ ላብ-አደር ህዝብ የጤንነት ደረጃ እናጠናለን፤እጅግ ዝቅ ያለ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እናሳያለን፤ የዚህም ሁኔታ አላፊ አድሀሪው መንግስት መሆኑን ባጭሩ እናመለክታለን።በመጨረሻም ተራማጅ ሀይሎች ያለውን ሁኔታ ሊለውጡ ስለሚችሉባቸው ዘዴዎች ጠቅላላ የሆነ አስተያየት እናቀርባለን።

የጤንነት ፕሮብሌሞች (ችግሮች) የሰውን ልጅ ከሚያጋጥሙት ብዙ ፕሮብሌሞች ውስጥ አንዱ ነው።ስለዚህ አንድ ህዝብ የጤንነት ፕሮብሌሞቹን ከሌሎች ፕሮብሌሞቹ ነጥሎ ሊመለከታቸው አይችልም። የተሟላ ፍችም ሊያገኙላቸው አይችልም።በዚህ በኩል የኢትዮጵያን ህዝብ ለሚያጋጥመው ችግር እውነተኛ መፍትሄውን የሚያገኘው ከፊውዳላዊው መንግስትና ከበላይ ተጠባቂው ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ላለው ተገራሪ ቅራኔ ፍች ሲያገኝለት ብቻ ነው።

ከዚህ በታች እንደምናየው የኢትዮጵያ ህዝብ የጤንነት ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ነው።ለዚህም ዋና ምክንያት የጤንነት ድርጅቶች ባለመስፋፋታቸው፤የበሽታ መከላከያ ባለመደረጉ፤ለህዝቡ የጤንነት ትምህርት ባለመሰጠቱና የውሀና የጠቅላላው አካባቢ ንፅህና በሚገባ ባለመጠበቁ . . . ነው።

የኢኮኖሚ እድገትና ጤንነት የተሳሰረ ግኑኝነት አላቸው።

ጤንነት ለኢኮኖሚ እድገት መንገድ ነው።የኢኮኖሚ እድገት ደግሞ የጤንነት ዋስትና ነው።ከኢኮኖሚ እድገት ግቦችም አንዱ ጤንነት ነው። እነዚህን አስተያየቶች ወንድም ይስሐቅ «የህዝብ ጤና ጥበቃ በባላባታዊው አገዛዝ» በሚል አርእስት ‹በትግላችን› ቁጥር 7 1960እ.ም. ባቀረበው ፅሁፍ ውስጥ በይበልጥ ተብራርተው ይገኛሉ።

1.የላብ-አደሩ የጤንነት ሁኔታ

ያንድን ህብረተ-ሰብ የጤንነት ሁኔታ በተቃረበ መንገድ ለማወቅ የሙቶችንናየበሽተኛውን ቁጥር፤የጤና ድርጅቶችን ስፋት መመልከት ይበቃል። እነዚህንም ቁጥሮች ከሌሎች አገሮች ወይም በአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት እንደመነሻ ተብለው ከሚሰጡት ቁጥሮች ጋር ማወዳደሩ ሁኔታውን በይበልጥ ያብራራል።

1. የሙቶችና የበሽተኛ ብዛት

በኢትዮጵያ ውስጥ እርግጠኛ የሆነ ቁጥር ለማግኘት ምን ያህል ችግር እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን።ከዚህ በታች የምንጠቅሳቸው ቁጥሮች ሁሉ የተቃረበ ግምት ለመስጠት እንጂ፤ እውነተኛውን ሁኔታ ያሳያሉ ለማለት አይደለም።ራሱን ያጥገሰ እየመሰለው፤የኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጠው ቁጥሮች ሁሉ እጅግ ተሻሽለው የሚቀርቡ ናቸው።ይህ ግብዝነት የኢትዮጵያንና የአለምን ህዝብ ለማታለል የታቀደ ነው። አንባቢው ይህንኑ በመገንዘብ እውነተኛው ቁጥር በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ከተሰጠው እጅግ የባሰ መሆኑን እንዲያስብ ያስፈልጋል።

ሀ) የሙቶች ቁጥር፤

የጤንነትን ደረጃ ለማወቅ ከሚረዱት ምልክቶች አንዱ የህፃናት—ከአንድ አመት በታች የሆኑ—ሞት ብዛት ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ ከሺህ ህፃናት ከመቶ-ሀምሳ እስከ ሁለት-መቶ ድረስ እንደሚሞቱ ይገመታል።በጐንደር ከተማና በአዲስ አበባ የተደረጉት ጥናቶች ይህንን ግምት አረጋግጠዋል። ታይባክና ረዳቶቹ በአምስት ከተማዎች ባደረጉት ጥናት ከሺህ ህፃናት መቶ አምሳ-ሁለቱ እንደሚሞቱ አረጋግጠዋል።ይህ ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በአመት ከሚወለዱት 950,000 ህፃናት መሀል ከ150,000 እስከ 190,000 የሚገመቱት አመት ሳይሞላቸ

ው ይረግፋሉ ማለት ነው። እነዚህ ጥናቶች ደግሞ የተደረጉት በየከተማው ስለሆነ በባላገሩ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚሞቱት ህፃናቶች ቁጥር ከፍ ያለ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

ይህ ቁጥር ምን ያሳየናል? ከዘመኑ የህክምና እውቀት መስፋፋት የተነሳ የህፃናት ሞት ከ1.5%(ከአንድ ነጥብ አምስት በመቶ) እንዳይበልጥ ለማድረግ መቻሉ ተረጋግጧል። በተለይም ይህን ቁጥር እስከ 3% ወይም 4% (ሶስት ወይም አራት በመቶ) ዝቅ ለማድረግ ብዙ ገንዘብ፣የተራቀቁ የህክምና ድርጅቶችና መሳሪያዎች አይጠይቅም። ስለዚህ የዚህ ቁጥር እጅግ ከፍ ማለት የሚያስረዳን ብዙ በቀላሉ መፍትሄ የሚገኝላቸው በሽታዎች ህፃኑን እንደሚፈጁት ነው።ማለት የህዝቡ ጠቅላላ የጤንነት ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ነው።የአንዳንድ አገሮችን ቁጥር ወስደን ስናወዳድር የተበዝባዥ አገሮች ሁሉ ከኢትዮጵያ ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ሲገኙ በሶሻሊስትና በኢምፔሪያሊስት አገሮች ግን የህፃናት ሞት በጣም ዝቅ ያለ መሆኑን እናያለን፡-

1. በልዩ ልዩ አገሮች የሚሞቱትን ህፃናቶች የሚያሳይ ቁጥር

የአገር ስም	እ.ም.	ከሺህ ጨቅላዎች የሞቶች ቁጥር
ኢትዮጵያ	1965	152
ማደጋስካር	1960	69
በርማ	1959	133.8
ህንድ	1959	87.9
ቺሌ	1960	132
ዴንማርክ	1959	22.5
ፈረንሳይ	1965	21.9
ካናዳ	1960	27

በምእራብ አውሮፓ ተቅማጥና ቅዝን ከህፃናቱ 1%(አንድ በመቶ)ብቻ ሲገሉ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት አገሮች ከ20%-25%(ከ

ሃያ እስከ ሃያ-አምስት በመቶ) ይፈጃሉ።
በቱይባክ ጥናት እንደተገለፀው በኢትዮጵያ ከሚሞቱት ህፃናት ውስጥ አራት በመቶው የተመጣጣ ምግብ ባለማግኘታቸው በረሀብ ያልቃሉ።

ለ)የበሽታ ብዛት

በማንኛውም ወደ ኋላ የቀረ አገር ስለበሽተኛና ስለበሽታ ብዛት ያሉትን ቁጥሮቹ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ችግር መሪነቱን ከያዙት አገሮች አንዷ ነች። ከዚህ በታች የምንጠቅሳቸው ቁጥሮች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የስታቲስቲክስ ክፍል የተሰጡ ሲሆኑ ባሰባሰባቸውም ሆነ ባያያዛቸው ብዙ ጉድለት አለባቸው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ቢያንስ ቢያንስ የተሰጡትን ቁጥሮች በአራት ማባዛት ያስፈልጋል (1)። በጠቅላላው ነገሩን ስንመለከተው በኢትዮጵያ እንደማንኛውም ወደኋላ የቀሩ አገሮች የበሽታዎቹ ዋና ምክንያቶች የወረርሽኝና፣የትል፣የተባይ ጠንቆች ናቸው።

2. በኢትዮጵያ ውስጥ የዋና ዋናዎቹ በሽታዎች ቅደም ተከተል ተራ(1962-1963)

በሽታ	ከሺህ ህዝብ	በሽታ	ከሺህ ህዝብ
ወረርሽኝና የትል	125	የወሊድ	4
የቆዳና ያጥንት	40	የሽንትና የብልት	4
የሳንባና የነቀርሳ	40	የደም	3
የስርችና የህዋሳት	29	ስራይ	2
የሆድና የአንጀት	29	የህሊና በሽታ	—
አደጋ	17	የህፃን አካል ጉደሎ	1
የምግብ	7	በወሊድ	C.5
እርጅና ወዘተ.	4		

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን መለየት አለብን።አንደኛ የበሽታና የሞት ቁጥር በጣም ከፍ ያለ ነው።አንድ ኢትዮጵያዊ በጉንደር በተደረጉት ጥናቶች መሰረት ለመኖር ያለው ተስፋ መካከለኛው ቁጥር 35

(1) ማብራሪያዎች የሚገኙት በፅሁፉ መጨረሻ ነው።

አመት ብቻ መሆኑን ማስታወስ ይበቃል። ሁለተኛ ደግሞ በተራመዱት አገሮችና በተበዝባዥ አገሮች መካከል ከፍ ያለ ልዩነት ይታያል። በኢትዮጵያ ከተባዮችና ከረሀብ የሚመጡ በሽታዎች ብዙ ሲሆኑ (ሰንጠረዥ ሁለት ተመልከት)በተራመዱት አገሮች በዝተው የሚገኙት ከመጠን የሚመጡ በሽታዎች—ካንሰር(ሲ.ራ.ይ?)፣የልብ፣ብዛደም ልርና የአንጉል—በሽታዎች ናቸው።በመጀመሪያው የበሽታዎቹ ምክንያቶች አለማወቅና ችግር ሲሆኑ፣በሁለተኛው ደግሞ የበሽታዎቹ ምክንቶች መትረፍረፍ መንደላቀቅ ናቸው። ከዚህ ሁኔታ ምን መረዳት ይቻላል?

—1ኛ.አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያ የሚገኙ በሽታዎች የምግብን ሁኔታ በማሻሻልና የአካባቢውን ንፅህና በመጠበቅ ሊሸነፉ ይችላሉ

—2ኛ.የነዚህ በሽታዎች መብዛት የህዝቡን የመስራት ችሎታና ጉልበት ይቀንሳል።ብዙውን ጊዜ ህይወቱን ሙሉ የሚቆይ አካለ ጉደሎነት ያስከትላል።ለህዝቡ ኤኮኖሚና ህብረተሰባዊ እድገት ትልቅ እንቅፋት ነው።

እንግዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ የበሽተኛውን መብዛትና ቀዳሚነቱንም የያዙት በሽታዎች በጣም በቀላሉ ሊጠፉ የሚችሉ መሆናቸውን፤የሀገሪቱም የጤንነት ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ባጭሩ አሳይተናል።ትክክለኛ የጤንነት ፖሊሲ ከተያዘ አብዛኛዎቹን የወረርሽኝ፣የተባይና የረሀብ በሽታዎች ለመቀነስና ለማጥፋት ይቻላል።እነዚህ የጤና ጠንቆች የሀገሪቱ ዋና ችግር ሆነው መቆየታቸው ያለው አስተዳደር ከጊዜው ሁኔታ ጋር የተጠናወተ ለመሆኑ ግልፅ ማስረጃ ነው።

2. ረሃብ

ኢትዮጵያ የእርሻ አገር ነች፤ኢትዮጵያ ለም ናት።በሀገሯችን ከ20 ሚልዮን በላይ የቀንድ ከብት፤ከ20 ሚልዮን በላይ በጐች፤ከ40 ሚሊዮን በላይ ዶሮ አለ ተብሎ ይገመታል።ይህ ሁሉ የሚያጠራጥር አይደለም።ሆኖም ኢትዮጵያ የረሀብ አገር ነች።ከህዝቡ ሃያ በመቶ በጣም ከፍ ባለ ረሀብ ያልታል(ረሀብ ስንል በድርቅ፤በአንበጣ...ወዘተ. ምክንያት«አልፎ አልፎ»የሚደርሰውን ፍፁም ማጣት አይደለም።ከቀን ቀን ከአመት አመት ሳይጠገቡ በመቅረት የሚመጣውን በሽታ ነው።)

«አመጋገብ ለሀገር መከላከያ» የሚባለው የአሜሪካን ክሚ

ቴ ለኢትዮጵያ መንግስት ባደረገው ጥናት እንደሚታየው (ሰንጠረዥ 3) በጠቅላላው አስተያየት እያንዳንዱ በቂ ኢትዮጵያዊ አመጋገብ ያለው መስሎ ይታያል።ሆኖም በዚሁ ጥናት እንደተገኘው ብዙ ኢትዮጵያዊያን ይራባሉ።

3. በየቀኑ ለያንዳንዱ ሰው የሚደርሰው ምግብ(የሚመረተው በነፍስ ወከፍ ተከፍሎ)

የምግብ አይነት	ኢትዮጵያ	ለአንድ ሰው አስፈላጊ ተብሎ የሚገመተው
ጠቅላላ ካሎሪ	2545.8	2700
ፕሮቲን(በግራም)	87	70–90
ዘይት ቅቤ(ግራም)	33	90
ካርቦ ሃይድሬት(ግ.)	462	450
ቪታሚን		
ኤ	1264.8	5000
ቢ	3.1	1
ሲ	6.5	70

4. በረሀብ(በአመጋገብ በሽታዎች)ይሰቃያል ተብሎ የሚገመተው ሰው ቁጥር በመቶ

በሽታው	ወንድ	ሴት
ከፍ ያለ መራብ	10	9
የፕሮቲን ማነስ	2	8
የቪታሚን መጉደል		
ሲ	33	33
ኤ	10	3
ቢ	3	3
ዲ	33	33
የደም ማነስ	6	19
እንቅርት	2	1

ሰንጠረዥ 4(የቀጠለ)

በሽታው	ወንድ	ሴት
ጥርስ በሽታ	23	23
ውፍረት	1	1
ደም ብዛት	3.2	24

ከሰንጠረዡ አራት እንደምንመለከተው

—1ኛ. ምንም እንኳን ከኢትዮጵያ ህዝብ ዘጠናው በመቶ በግብርና ስራ ላይ ቢሰማራ፤ምንም እንኳን ሀገሪቱ ለምለምና ለልዩ ልዩ ምርት የተመቸች ብትሆን፤ጠቅላላው ምርት ከሀገሪቱ ፍላጎት ጋር ጨርሶ አይመጣጠንም።እንደውም ድር ወደ ውጭ ይሸጥ የነበረው ህዝብ አሁን የስንዴ ምፅዋት ተቀባይ ሆኗል። (2ኛውን የአምስት አመት ፕላን ተመልከት)

—2ኛ. ያለውና የሚመገበው ሀገሪቱን በልኩ ሊያጠግባት የሚችልም እንኳን ቢመስል፤ ጥቂቶች ዘራፊዎች በአብዛኛው ማጣትና መራብ ላይ ስለሚንደላቀቁ ከህዝቡ ሩቡ በቂ ምግብ አያገኝም።

—3ኛ· የማጣትና የመራብ ሁኔታ የሚያደርስበት የሀብቱና የምርቱ ምንጭ የሆነው ሰራተኛና ገበሬ ነው።በዚህም ክፍል ውስጥ በተለይ ህፃናቶቹ ናቸው።የሰውነታቸው እድገት እጅግ ይቀንሳል።ቁመትና ክብደታቸው በጣም ዝቅ ያለ ነው።በሽታ በቀላሉ ያጠቃቸዋል።የአእምሮ እድገታቸው ይደናቀፋል።ለስራ ያላቸው ችሎታና ፍላጎት በጣም አነስተኛ ነው. . .።ይህ ሁኔታና መዘዙ በቀላሉ አይገመትም።

II.የጤንነት ደረጃ

ለጊዜው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የጤንነት ድርጅት በሰው(ሀኪም፤አስታማሚ፤መድሀኒት ቀማሚ ...ወዘተ.) ሆነ በእቃ(በአልጋ፤መድሀኒት ...ወዘተ.) በጣም ዝቅ ያለ መሆኑን ሁላችሁም እናውቃለን።ሁኔታውን በቁጥር እንየው

1.የጤንነት ድርጅት ሰራተኞች (ፔርሶኔል)

ሰንጠረዥ 5ን(ገፅ 18 እና 19) አጢኑን እንመልከት፡—

1ኛ. ጠቅላላ አስተያየት

እ.አ.አ. በ1965 እ.ም. ኢትዮጵያ ከ24 እስከ 25 ሚልዮን ለሚገመት ህዝብ 324 ሀኪሞች ብቻ ነበሯት። ይህም ለ175,000 ሰው አንድ ሀኪም እንኳን አልነበራትም ማለት ነው። ይህ ሁኔታ እ.አ.አ. በ1968 እ.ም.ተሻሽሎ አይታይም።«Jeune Afrique» በ1968 እ.ም.ባወጣው ማስረጃ መሰረት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አገሮች ውስጥ ከመጨረሻው ሁለተኛውን ቦታ ይዛለች፤ከሌላው አገር ጋር ጨርሶ ማወዳደር አይቻልም።ለማስታወስ ያህል የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት አንድ ሀኪም ለ700 ሰው በቂ መካከለኛ ቁጥር ነው ተብሎ ይገመታል።አንዳንድ አገሮች ከዚህም የተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።(ለምሳሌ በሶቪየት ህብረት ለ450 ሰው አንድ ሀኪም ነው።)

አስታማሚዎችንና ረዳቶቻቸውን፤የጥርስ ሀኪሞችንና መድሀኒት ቀማሚዎችን የወሰድን እንደሆን ሁኔታው ያው በሀኪሞች በኩል እንዳየነው ነው፤ እንዲያውም አንዳንዱ ይብሳል።ዝቅ ብለን ሰንጠረዡ ስድስትን ብንመለከት ኢትዮጵያ ወደኋላ ከቀሩት አንዳንድ አገሮች (ለምሳሌ ሲሎንና ቺሌ) እንኳን ልትመሳሰል አትችልም። የኢትዮጵያ ሁኔታ የባሰ እንደሆነ በግልፅ ለመረዳት ይቻላል።ለማነፃፀር ያህል በአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ግምት መሰረት የአስታማሚዎች ቁጥር አጥጋቢ ነው ሊባል የሚቻለው በመካከለኛው ቁጥር ለ300 ሰው አንድ አስታማሚ ሲኖር ነው።

2ኛ. ጉዳዩን በጠቅላላ አስተያየት ላይ ላዩን ተመልክተን

— የህዝብ የጤንነት ሁኔታ በጣም አሳሳቢ መሆኑን

— የጤንነት ድርጅቶችና የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ከቁጥር የማይገቡ መሆናቸውን ተረዳን

ወደ ውስጥ ገባ ብለን ብንመለከት ደግሞ ሁኔታው ቁጥሮቹ ከሚያመለክቱት የራቀ ሆኖ እናገኘዋለን።የላብ አደሩ ሁኔታ ቁጥሮቹ ለማሳየት ከሚጥሩት የጤንነት ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ነው፤እውነቱ ከሚለፈፈው የአይን መሸፈኛ ፕሮፓጋንዳ የራቀ ነው።

በ1965እ.ም. ከ324ቱ ሃኪሞች ውስጥ 156ቱ ማለት ወደ

በጠቅላይ ግዛቶችና የጤና ጥበቃ ሠራተኞች በኢትዮጵያ

ምንጭ፡- የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ጤና ጥበቃ በኢትዮጵያ 1965

	አዲስ አበባ	አሩሲ	ባሌ	በጌምድር	ኤርትራ	ጋሙ ጎፋ	ጎጃም	ሀረርጌ	ኢሉባቦር	ከፋ	ሸዋ	ሲዳሞ	ትግሬ	ወለጋ	ወሎ	ጠቅላላ ድምር	
ሐኪም	156	2	1	11	68	3	5	27	3	6	16	7	8	6	5	324	Doctors
አስታማሚ	283	13	4	14	81	2	3	31	3	10	15	12	5	26	12	514	Nurses graded
የጤና ኦፊሰር	22	3	1	6	5	4	7	10	8	5	11	4	6	6	7	105	Health officers
የመንደር አስታማሚ	14	3	–	11	6	–	5	6	6	3	12	4	10	6	4	90	Community nurses
የጤና ቴክኒሺያን	9	4	1	9	3	4	8	8	8	5	14	4	10	7	6	100	Sanitarians
ረዳት አስታማሚ	248	22	11	30	330	10	15	80	25	18	120	70	35	40	36	1090	Advanced dressers
ጀማሪ ረዳት አስታማሚ	170	64	12	70	–	19	45	135	50	96	229	145	100	155	85	1375	Elementary dressers
መድኃኒት ቀማሚ	8	–	–	–	5	–	–	2	–	–	–	–	–	–	–	15	Pharmacists
ረዳት መድኃኒት ቀማሚ	21	–	–	–	–	–	–	2	–	–	2	–	–	–	1	27	Assistant Pharmacists

50%(አምሳ በመቶ) ገደማ በአዲስ አበባ ውስጥ ነበሩ። የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት በ1960 እ.ም. ባደረገው ጥናት እንዳገኘው ከ100,000 ህዝብ በላይ ባላቸው ሁለት ከተማዎች(አዲስ አበባና አስመራ) ለ2720 ሰው አንድ ሀኪም ሲኖር፤በተቀረው አገር ውስጥ ለ191,400 ሰው አንድ ሀኪም ብቻ ነበር።በአሩሲ፤በባሌ...ወዘተ. ሲባል ደግሞ(ሰንጠረዥ 5)እ ዉቃኛውን ጊዜ በዋናው ከተማ ማለት ነው።እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱትን የማይከድና መራራ እውነት ስለድርጅቱ በምንሰጠው ጠቅላላ መደምደሚያ ላይ እናያለን።እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባን ከዘጠና በ መቶ በላይ የሚሆነው ገበሬ ህዝብ የሚኖረው በገጠር መሆኑን ነው።

6. የጤና ድርጅት ሰራተኞች(እ.ኢ.አ.1959)

ሀገር	የሰው ቁጥር ለአንድ			
	ሀኪም	መድሀኒት ቀማሚ	አስታማሚ	ጥርስ ሀኪም
ኢትዮጵያ	60.000	1.333.000	20.000	400.000
ሲሎን	4.600	10.300	6.400	59.000
ቺሌ	1.700	3.700	630	3.100
ሰሜን አሜሪካ	790	1.000	300	1.900
እስራኤል	420	1.900	400	1.400
ስዊድን	1.100	3.500	120	1.000
ቼኮዝሎቫክ	640	2.900	300	3.180

ምንጭ፡-የጤና ጥበቃ ድርጅት በ1963እ.ም. ካወጣቸው ስታቲስቲኮች በኢትዮጵያ አስታማሚ ሲባል ነርሶችንና ከፍተኛ ድሬሰርችን ይጠቀልላል።

2. የጤንነት ድረጅት—እቃዎች

የጤና ጥበቃ ሚንስቴር እ.አ.አ.በ1967 እ.ም. መጨረሻ ላይ ባወጣቸው ስታቲስቲኮች እንደሚታየው በሀገሪቱ 8,830 አልጋዎች የያዙ 83 ሆስፒታሎች አሉ፤ማለት ለ10,000 ሰው አራት አልጋ እንኳ የለም።ከሌሎቹ አገሮች ጋር ሲተያይ ይህ መጠን በዝቅተኛነቱ ተወዳዳሪ የለውም።ለምሳሌ እ.አ.አ. ወደ 1960 እ.ም.ገደማ (ማለት ለኢትዮ

ጵያ ከመለከትነው ጊዜ ሰባት አመት ቀድሞ) ቀጥሎ የተጠቀሱት አገሮች ለ10,000 በሰንጠረዥ 7 እንደሚታየው ነበር።

አገር	አልጋ ለ10,000 ሰው	አገር	አልጋ ለ10,000 ሰው
ኢትዮጵያ	3.7	ኢንዶኔዚያ	8.4
ናይጄሪያ	4.7	ፈረንሳይ	110
ኮሎምቢያ	49	ስዊድን	156

ከፍ ብለን እንዳየነው አገራችን በርግጥ በጤና ጥበቃ ድርጅት በኩል በጣም የተራቆተች ናት።እውነቱ ግን ይህ ብቻ አይደለም፤የ ተሰጡት ቁጥሮች የሳብ አደሩን እውነተኛ ሁኔታ ይደብቃሉና።ያው ያ ለው ትንሹ የጤና ድርጅት የሚያገለግለው እጅግ ለማይጥሩ ገራፊዎ ች መሆኑ ብቻ ነው።እንዲያውም ለገጠሬውና ለሰራተኛው የሚያደ ርሰው ድርጅት ከዚህም በጣም ዝቅ ያለ ነው።

—44%(አርባ አራት በመቶ)የሚሆነው አልጋ የሚገኘው ከሆሀ ሁ 3%(ሶስት ከመቶ)በማይኖርበት በአዲስ አበባና በአስመራ ከተሞች ውስጥ ነው።ከተረፉትም አብዛኞቹ አልጋዎች ያሉ ት በየጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተሞች እንደሆነ ጥርጥር የለውም ከ90%(ከዘጠና በመቶ) በላይ ለሆነው በገጠር ኗሪ የኢትዮጵ ያ ገበሬ የሚተርፉት አንዳንድ የውጭ አገር ሚሽኖች የሚ መፀውቱት ወደ አንድ ሽህ የሚጠጉ አልጋዎች ናቸው። ያው ም ቀፈፋው ተሰክቶለት ሊጠቀምባቸው የቻለ እንደሆ !

—በጠቅላላው በአገሪቱ ካሉት ሆስፒታሎች ውስጥ አምስቱ ማ ለት 6%(ስድስት ከመቶው)የ«ድሀ ሆስፒታሎች›ናቸው።(በ በጐ አድራጐት ስም በቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ የንግድ ድርጅት ስ ር ይተዳደራሉ»)።ከነዚህ ሆስፒታሎች ሶስቱ በአዲስ አበባ፤አን ዱ በሀረር፤ቀሪው በትግሬ ውስጥ ይገኛሉ።በሙሉ ያላቸው የአ ልጋ ቁጥር 791፤ማለት 9%(ዘጠኝ በመቶ) ነው።

በሰራተኛና በእቃ በኩል ላለው የጤንነት ድርጅት ሀኪሞ ችንና ሆስፒታሎችን ብንወስድ ቁጥራቸው በጣም ዝቅ ያለ ከመሆኑም በላይ፤እነዚያው ያሉት የተከማቹት በትላልቅ ከተማዎች ውስጥ ነው።በ

ዚህ ሁኔታ ግን ሊጠቀምባቸው ይችላል? እንደምናውቀው በኢትዮጵያ በጣም ከፍ ያለ የመገናኛ መንገዶች ችግር አለ፤በተጨማሪ የገበሬው ህዝብ የገንዘብ እጦት ለማንም ግልፅ ነው።በዚህ አኳኋን ያሉት የህክምና ድርጅቶች ለሰፊው ህዝብ አገልግሎት እንዲሊታሰቡ ለመረዳት ብዙ ማስረጃ አያስፈልገንም።በነፃ የሚያክሙ የድሀ ሆስፒታሎችና በከተም ውስጥ የሚሰሩት ሀኪሞች በጣም የተወሰኑ ናቸው(6%)።በሌሎች ሆስፒታሎች ለመታከም መክፈል ግዴታ ነው።

ታዲያ ከተሞችስ ውስጥ ከፍሎ ለመታከም የሚችለው ስንቱ ነው? ማንስ ነው? በማንኛውም ሆስፒታል የመጀመሪያውን ዝቅተኛ ምርመራ ለማድረግ ከ1.50 ብር እስከ 2 ብር መክፈል ያስፈልጋል። በዚህ ላይ የአይነ ምድር፤የሽንት፤የደም ወዘተ. ምርመራ የተደረገ እንደሆነ ጭማሪ መክፈል አለበት።ማለት ማንኛውም ቀላል በሽታ(ሆስፒታል ውስጥ መተኛት የማይጠይቅ፤ለመድሀኒት አንድ ብር ብቻ እንኳ ይበቃል ብንል፤ከ2.50 እስከ 3 ብር ወጪ ይጠይቃል።ግን ምርመራና መድሀኒት መደጋገም ካለበት፤ሆስፒታል መተኛት ካስፈለገ ወጭውን በ20 ወይም በ30 ማባዛት ያስፈልጋል።) —ማስያዣው ከ20 እስከ 40 ብር ነው—።

በአዲስ አበባና(በኢትዮጵያ ስዊድሽ የህፃናት ክሊኒክ) በጐንደር(በጤና ጥበቃ ኮሌጅ) ስለወላጆች የኑሮ ሁኔታ የተደረጉት ጥናቶች እንደሚያሳዩን

— አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች በወር ቋሚ ገቢ የላቸውም
— የአዲስ አበባ ቤተሰቦች 55%(አምሳ አምስት በመቶ)የወር ገቢ ያቸው ከ25 ብር በታች ነው።
— የአዲስ አበባ ቤተሰቦች 80%(ሰማኒያ በመቶ) የወር ገቢያቸው ከ50 ብር በታች ነው።
— በአብዛኛዎቹ የኢኮኖሚ ክፍሎችና ስራዎች በደምወዝ በኩል ጭማሪ ሳይኖር የህክምና ወጪ በጣም እያደገ ሄዷል(ለምሳሌ በአዲስ አበባ የህክምና ወጪ ከ1963 እስከ1967(እ.አ.አ.)አድጓል።(ስለሰራተኞች ደምወዝ«ትግላችን» ቁጥር 8 እ.አ.አ. 1960 ኢ.ም.ውስጥ የሚገኘውን ፅሁፍና «Economic Review»1968 ተመልከት።)

የጐንደር ጥናቶች ተመሳሳይ ቁጥር ይሰጣሉ። በተጨማሪ የኢትዮጵያ ቤተሰብ የሚይዘው መካከለኛ ቁጥር አራት ሰው ነው።ከከተማው ሰው ሰማኒያ በመቶ ከአምሳ ብር በታች በሆነ ገቢው የአራት ሰው ምግብ፤ልብስ፤የትምህርት፤የጤንነት...ወዘተ.መቻል አለበት ማለት ነው።ከላይ ያየነው የህክምና ወጪ በዚህ ገቢ እንደማይቻል ግልፅ ነው። እንግዲያው ከሚከፈልባቸው ሆስፒታሎች ቢያንስ ቢያንስ 94% (ዘጠና አራቱ በመቶ)ከከተማው ህዝብ ለ80%(ለሰማኒያው በመቶ)አልታሰቡም ማለት ነው።ይህን በከተማ ኑዋሪ ላብ አደር ህዝብ የሚጠባበቀው «የድሀ ሆስፒታሎች» የሚወረውሩለትን የህክምና ምፅዋት ነው።እነዚህ ሆስፒታሎች የመሞቻ ጉድጓዶች እንጅ የመታከሚያና የመፈውሻ ቦታዎች አለመሆናቸውን እየተንጠባጠቡ የሚገቡት በሽተኞች ሁኔታ በግልፅ ያሳያል።

በበሽታ ተከራምቶና በሞት አፋፍ ላይ ተንጠልጥሎ ሳለ ለድህነትህ ሳስት ምስክሮች ጥራ እየተባለ የሚሰቃየውና በ«በጐ አድራጐት» ስም ታክመሀል (መታከም ብለን ልንጠራው ብንችል) እየተባለ የሚሸኘው ህዝብ በድካሙና በላቡ ለሀገሪቱ ገቢ ምንጮች አንዱ የሆነው የከተማ ሰራተኛ ነው።«ድህነት ወንጀል» በሆነባት ድሀይቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ተነፍጉት በረሀብና በበሽታ አለንጋ የሚገረፈው ሰርቶ አደርና ምስክር የሌለው ህዝብ እየታፈሰ የሚሄደው ላምበረትና ይህን በመሳሰሉ ኢ-ሰብአዊ ማጉሪያዎች እንጅ ወደ ሆስፒታል እንዳልሆነ እናውቃለን።ለድሀ የተመደቡት ሆስፒታሎች እነዚህ በረቶች ናቸው።የ«በጐ አድራጐት» የሚባሉት ሆስፒታሎች ስራ ለተነፈገውና ለአከለ ጉደሎው ያልታሰቡ፤ችሮታቸውና በጐ አድራጐታቸው ጋር የተቀባ መርዝ ናቸው።ግን ከቀን ወደ ቀን እየተረዳው የሚሄደውን ሰራተኛና ገበሬ ለማታለል አይችሉም።

ነገሩን ለማጠቃለል ያህል

— የላብ አደሩ የጤንነት ደረጃ በጣም ዝቅ ያለ ነው።
— የላብ አደሩ የጤና ማጣት ዋና ምክንያት ወረርሽኝና ከተባይ የሚመጡ በሽታዎች ስለሆኑ፤እነዚህ በሽታዎች በጊዜው የሳይንስ እውቀት በቀላሉ ለመሸነፍ የሚችሉ ናቸው።

— በዕውም ሆነ በኢታ በኩል ያለው ድርጅት በጣም ዝቅ ያለ ነው
— ያሉትም ጥቂት የመታከሚያ ድርጅቶች የተከማቹት በትላልቅ ከተማዎች በተለይ በአዲስ አበባና በአስመራ ስለሆነ ከኢትዮጵያ ህዝብ ዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነው ሰራተኛና ገበሬ ሊጠቀምባቸው አይችልም፤እንዲጠቀምባቸውም አልታሰበም።
— በከተማዎችም ውስጥ ያሉት ድርጅቶች ላላቸው እፍኝ ለማይሞሉ መታከሚያና ማረፊያ ቦታ እንጅ ለጠቅላላው ህዝብ በተለይም ለሰርቶ አደሩ ክፍል አገልግሎት ሊውሉ አይችሉም።
— ያለው አገዛዝ ገዥ፤ሀይሉን የጨበጡትን እፍኝ የማይሞሉ የመኳንንት የመሳፍንት የዘረፋ መብት መጠበቅና ድሎታቸውን በህዝብ ጀርባ ላይ ማዳበር ስለሆነ፤ለህዝቡ ጤንነት ሁኔታ መፍትሄ የሚሆን አቋም አይወስድም፤በባህሪው ወደ ኋላ ተመልካች በመሆኑ ይህ ሁኔታ እንዲለወጥ አይፈልግም። ሁልጊዜ የሚያሰናዳው የጤንነት ድርጅት ለጥቂቶች መቀናጣ ብቻ ነው። ሰፊውን ህዝብ ግን «የበጐ አድራጐት፤የድሆች መረዳጃ ...ወዘተ.» እያለ በሚያቋቁማቸው የንግድ ድርጅቶች ደልሎ ሊሸፍናቸው ይፈልጋል። ስለዚህ ባለው አቋም ውስጥ ለወደፊት የተሻለ ሁኔታ ይፈጠራል ማለት አእምሮ ቢስነት ነው፤እውነተኛውን መፍትሄ መፈለግ በሌላ አቋም ውስጥ ነው፤ይህ መፍትሄ ምን ሊሆን ይችላል።

III. መፍትሄ

የጤንነት ጉዳዮች ተራማጅ ሀይሎች ሁሉ በቀደምትነት መፍትሄ ሊፈልጉላቸው ከሚገባቸው ጉዳዮች መካከል መሆናቸውን ቀደም ብለን ተናግረናል፤በሚቀጥሉት መስመሮች የዚህን መፍትሄ ጠቅላላ ይዘትና አንዳንድ የሚያስከትላቸውን ጥያቄዎች እናያለን።

ዘላቂ እንዲሆን የሚፈለግ መፍትሄ ባልተጨበጠ ሀሳብና በባዶ ሜዳ ላይ አይቀየስም፤ባለው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚመጣከለው ሁኔታ ፈልቶ የሚያድግ መሆን አለበት፤ሁኔታውንም በደንብ ለመረዳት እስከሁን ያመራባቸውን የታሪክ ጉዳናዎች ከሁሉ ማእዘን ማየት

ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ በጣም የቆዩና ጊዜ የፈተናቸው ብሄራዊ የህክምና ዘዴዎች አሏት፤እርግጥ እነዚህ ዘዴዎች ብዙ ከንቱ እምልኮቶችንና ያንኑ ያህል ከንቱ የሆኑ ብዙ መንፈሳዊ እስተያየቶችን አዝለዋል፤ቢሆንም እነዚህን ጥንታዊ ብልሃቶች ከጊዜው ሳይንሳዊ እውቀቶች ጋር በማዋሀድ ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በበለጠ ተስማሚ የሆነ የጤንነት ድርጅት ለመፍጠር እንደሚቻል እናምናለን።

ዘመናዊ የህክምና ድርጅት ወደኢትዮጵያ ከገባ ብዙ ጊዜ አላለፈም፤በ19ኛው መቶ አመት ሚሲዮናች አንዳንድ ሆስፒታሎችን መክፈት ጀመሩ፤ወዲያውኑ የመጀመሪያዎቹ የጤና ህጐች ወጡ፤ጣሊያን አገሪቱን ከመውረሩ በፊት ወደ 12 ሆስፒታሎችና(4 በአዲስ አበባ) 2 የአካለደዊ ህክምና ቤቶች፤በአገሪቱ ዋና ዋና ከተማዎች ውስጥ ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ያለውን ሁኔታ አይተናል፤ጉልቶ የሚታየው ያሉት የጤና ድርጅቶች በከተማ መከማቸታቸውና እፍኝ ለማይሞሉ መኳንንትና መሳፍንት መቀናጣ እንጂ ለሰፊው ህዝብ አገልግሎት ያልታሰቡ መሆናቸው ነው።

አሁን ያሉት ባለስልጣናች ይህን ሁኔታ ሊለውጡት ይችላሉ ወይ ለሚለው ጥያቄ የምናገኘው መልስ ያለጥርጥር አሉታ ነው፤አድሀሪው መንግስት በዚህ በኩል የሚያስፈልጉትን ለውጦች ለማምጣት ፍላጐቱም ችሎታውም የለውም፤ውስጣዊ ጠባዮቹ በመሰረታቸው እውነተኛ ለውጥን ለማምጣት አይፈቅዱለትም። ስለውስጣዊ ጠባዮቹ እንደገና ቦታ ውስጥ መግባት የሚያስፈልግ አይመስለንም፤ለይስሙላና ባፍ ለመደለል አድሀሪው መንግስት ብዙ ማስወራቱ አይቀርም፤ለምሳሌ በ1952 ለገጠሩ ህዝብ ልፎ ልፎ የጤና ጣቢያዎችን በሰፊው ለማቋቋም ነው ሲል አስወራ፤የገጠሩ ኑሮ ግን ታክስ ከሚከፈልበት ጊዜ በስተቀር ከዚያ በፊት ስለጤንነት ሲወራ ሰምቶ አያውቅም። ተከታትለውም የወጡት የአምስት አመት ፕላናች ለህዝቡ ጤንነት ተቆርቋሪ መሆናቸውን በሰፊው ገለፁ። ለምን? ለማያውቀው ጤንነት ግብር መከፈል የተንገፈገፈውን ህዝብ ለማስታገስ፤ለይስሙላ ለውጭ ፖለቲካው እንዲመቸውና በህዝቡ ስም አገሪቱን በገንዘብ ለመሸጥ እንዲመቸው

ነው። ይህ ወሬ አሁን የት ደረሰ? ከአስራ ሰባት አመታት በኋላ በአገሩ
ውስጥ 64 አፀደ ማቢያዎችና ወደ 500 የሚሆኑ ንኡስ ማቢያዎች አሉ
አብዛኞቹ አገልግሎታቸው በጣም የተወሰነ ነው።ለማንኛውም ከአገሪቱ
ፍላጐት ጋር ሲወዳደሩ እንደሌሉ መቁጠር ያቻላል።ቀጥለውም የወጡ
ት ፕላኖች የሚሉት ለሚቀጥለው ጊዜ ይሰራል ነው። «ከልብ ካለቀሱ
እምባ አይገድም» እንደሚባለው ሁሉ በወነት ታስቦበት ቢሆን በ17አ
መታት ውስጥ...።በዚህ አይነት 50 አመትም ቢቆይ የጤና ፕሮብሌም
መፍትሄ ሊገኝለት አይችልም።

እንግዲያውስ እውነተኛው መፍትሄ ከባላባታዊው መንግስ
ት አጽም ውጭ መፈለግ አለበት።ስለዚህ ነው ከመጀመሪያው የጤንነት
ን ጉዳይ ከሌሎቹ የህዝብ ፕሮብሌሞች ለይተን ማየት አንችልም ያልነ
ው።ለኢትዮጵያ የጤንነት ችግር መፍትሄ የሚገኘው ህዝቡ ከባላባታዊ
ው መንግስትና ከፀባይ ጠባቂው ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ላለ
ው መሰረታዊ ቅራኔ ጠቅላላ መፍትሄ ሲያገኝ ብቻ ነው።

ይህ መፍትሄ ከህዝቡ የብዙ ጊዜ ድርጅትንና ትግልን እን
ደሚጠይቅ አይጠረጠርም።ህዝቡ በዚህ ትግል ውስጥ በየጊዜው ለሚ
ያጋጥሙት ችግሮች ሁሉ ተገቢውን መፍትሄ የሚያስገኙለትን ድርጅ
ቶች ያዳብራል።ከነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የጤና ድርጅቶች ተገቢ ቦታ
ቸውን ይዘው ከትግሉ ጋር ያድጋሉ። ትግሉ የሚወስዳቸውን ልዩ ልዩ
መልኮች፣የሚሄድባቸውን ልዩ ልዩ ጊዜዎችና ቦታዎች የሚከናወንባቸ
ው፡ ልዩ ልዩ ፍጥነቶችና ሀይሎች ከሁኑ ለመገመት በጣም አስቸጋሪ መ
ሆኑን እናውቃለን።በብዙ ጊዜያዊና ቦታዊ ሁኔታዎች መለዋወጥ ላይ ለ
ሚመሰረቱ እንቅስቃሴዎች ፍፁም የመጨረሻ መልክ ከሁኑ ለመስጠት
መሞከር ከንቱ ውዳሴ ነው።ከሁኑ ለማወቅ የምንችለው የዚህን መፍት
ሄ ጠቅላላ መሪ ሀሳቦችና ዋና ዋና መልኮች ብቻ ነው።

ይህ መፍትሄ በህዝቡና በግንባር ቀደም ድርጅቱ መካከል ባ
ለው ጥብቅ ግንኙነት ላይ መመስረት አለበት።ህዝቡ የጤንነት ምኞቶቹ
ን፣ ፍላጐቶቹን፣ ችግሮቹን፣ ለመልካም ጤንነት የሚያስፈልጉትን ነገ
ሮች ማወቅና ማስታወቅ፣ መግርና ማስተማር፣ ለችግሮቹ መፍትሄዎች
አስፈላጊውን ግዴታዎች መፈፀምና ማስፈፀም የሚያስችሉትን ሁኔታ

ዎችና ድርጅቶች ከመሪዎቹ ጋር በመመካከር መፍጠር አለበት።መሪዎ
ቹ የህዝቡን የጤና ፍላጐቶች በማጥናት ትክክለኛውን ትርጉም መስጠ
ት ይኖርባቸዋል።ከላይ እንዳልነው ትግሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ በአይነቱም በ
መልኩም ሲለዋወጥ፤ በህዝቡና በፀረ-ህዝቡ መካከል ያለው የሀይል ሚ
ዛን ታሪካዊ ግዴታውን በመከተል ወደ ህዝቡ እያመዘነ ሲሄድ፤ ከዚያም
ህዝቡ አሸንፎ ህዝባዊ መንግስት ሲቆም፤ መፍትሄው በአይነቱም ሆነ በ
መልኩ መቀያየሩ አይጠረጠርም።ግን ምንም ጊዜ ቢሆን በእውነተኛ የህ
ዝብ ፍላጐት ላይ የተመሰረተና ህዝባዊ ይሆናል።

ቢጫሩ ድርጅቶቹና ድርጊቶቹ ለጠቅላላውና ለሰፊው ህዝብ
የታሰቡና የሚደርሱ ይሆናሉ።ለዚህም ሰፊው ህዝብ ለአካባቢ፣ለራሱና ለ
አመጋገብ፣በሽታን ለመቀነስና ለማጥፋት፣ የታመሙትን ለመፈወስና ለ
ማዳን በሚደረገው ዘመቻ እንዲካፈል ይደረጋል።ህዝቡ ለነፃነቱ በሚ
ታገልበት ጊዜ ለሚነሱት የጤንነት ችግሮች መፍትሄ መፈለግ፣አዲስ ተ
ስማሚ የመከላከያና የማከሚያ ዘዴዎች እንዲሁም ለትግሉ የተዘጋጁና
ጠቃሚ በሚሆንባቸው ዘዴዎች መጠቀም ይኖርበታል።

ለኢትዮጵያ የጤንነት ችግሮች እውነተኛው ህዝባዊ መፍ
ትሄ ጠቅላላው መልኩና ድርጅቱ ምን አይነት ሊሆን እንደሚችል ለማ
ሳየት ሞከርን።በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የጤንነት ደረጃ ምን ያህል ዝ
ቅ ያለ መሆኑን አይተናል።የትግሉን ትልቅነት ማንኳሰስ ሀሰተኛነት ነ
ው፤ ግን ማየት ያለብን መውጫዎቹ መንገዶች የማያዛልቁ መሆናቸው
ን ነው።

ወረርሽኝንና የተባይ በሽታዎችን ከፍ ባለ አኳሆን ለመቀነስ
የመጀመሪያው እርምጃ የግልን፣ የአካባቢንና የአመጋገብን ንፅህና ማ
ሻሻል ነው።የረሀብን (በስጠነው ትርጉም መሰረት) በሽታዎች ለማጥፋ
ት፣ምርቱን ማሻሻልና ህዝቡ የምግብ አመራረጡን እንዲያሻሽል ማድ
ረግ ነው።

እነኝህ መፍትሄዎች በገንዘብና በቴክኒክ በኩል የሚጠይቁ
ት ወጭ በጣም ዝቅ ያለ ነው። የውጤታቸው ግግር ዋና መሰረቱ፣ህዝ
ቡ ትግሉ (ዘመቻው) የራሱና ለራሱ መሆኑን ተገንዝቦት፣በሙሉ እም
ነት፣ፈቃድና ልብ መሳተፉ ነው።ይህንን ሙሉ እምነት፣ሙሉ ተሳታፊነት

ማግኘት የሚችለው ህዝባዊ መንግስት ብቻ ነው።የአሁኑ መንግስት ሁኔታው ከቀን ወደቀን እየባሰ ሲሄድ መፍትሄ ለማቅረብ ያልቻለውና የማይችለው ህዝቡን በሙሉ እምነት ለማሰለፍና ለመምራት ስለማይችል ነው።

እነኚህን ችግሮች ህዝቡ በህዝባዊ መንግስት ስር በተፋጠነ ሁኔታ ሊያሸንፋቸው እንደሚችል የሶቪየት ህብረት፣ቻይናና ቪየትናም ... ታሪካዊ ምስክሮች ናቸው።የኢትዮጵያ ህዝብ ከሌላው ህዝብ ይልቅ ደደብ፣ግድየለሽ፣ፈሪና ሰነፍ ነው ብለው ሊያሳምኑ የሚሞክሩት በሱ ድካምና ልፋት ያለሀሳብ የሚንደላቀቁት መኳንንትና መሳፍንት ብቻ ናቸው።ሰነፍ፣ፈሪ፣አጭበርባሪና ከሀዲ ቢኖር እነሱ ናቸው።የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ ግንባር ተደራጅቶ ሀይሉን መጥና የሚነሳበት ቀን እንደተዳረሰ ብዙ ምልክቶች አሉ።የያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ተግባር ለዚህ ቀን ተደራጅቶ መገኘትና ቀኑም ቶሎ የሚደርስበትን ሁኔታ ማዘጋጀት ነው።ያን ጊዜ ሁሉም አብሮ የኢትዮጵያን የጤንነት ችግር ይፈታዋል።

ስለኢትዮጵያ የጤንነት ሁኔታ አንዳንድ ምንባቦች (የመፅሀፍ ዝርዝር)

— «An Introduction to Health and Health Problems in Ethiopia»; Edited by E.F. Tourey: Artistic Printers Ltd Addis Abeba,1967 (በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የጤንነት ሁኔታ ብዙ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን የያዘ ነው።)

— «Interdepartmental Comittee on Nutrition for National Defence, U.S.A.፡Ethiopia, Nutrition Survey 1959 (በኢትዮጵያ ስላለው የምግብና የአመጋገብ ሁኔታ ጠቃሚ ጥናቶች አሉበት።)

— Brown A.E.; The Health Situation and Problems in Ethiopia 1966—Paper designed to assist in the formation of the third five year plan — Addis Abeba

1967 (አልታተመም፣መንግስቱ መሰራጨቱን ስላልወደደ በቀላሉ እንዳይገኝ አድርጓል።የያዛቸው መረጃዎች በጣም ጠቃሚዎች ናቸው።)

— Wen-Pin Chang, M. D. "General Review of health and medical problems in Ethiopia". (Ethiopian Medical Journal 1962 Vol. 1,No.1)

— Spruyt, D. Jetal "Health Center Programme" (Ethiopian Medical Journal 1967,Vol.5, No.3)

የኢትዮጵያን የጤንነት ሁኔታ በጠለቀ አኳኋን ለማወቅ የሚፈልጉ ሁሉ፦
  - The Ethiopian Medical Journal
  - Gondar Health Series

ልዩ ልዩ ቁጥሮች ቢያነቡ ጠቃሚ ማስረጃዎችን ያገኛሉ።

— በመፍትሄው በኩል፦
  - "Medical Care in Developing Countries, a symposium from Makarere" (Edited by Maurice King,Oxford University Press,Nairobi,1966) እና "Public Health in U. S. S. R", (WHO Public health Papers,No. 11, 1966)
  - "Problémes medico-sanitaires au Nord Vietnam" (Etudes Vietnamiennes,No.8)

የኢትዮጵያ ላብ-አደር ህዝብ ሁኔታ

(በ16ኛው መቶ አመት)

ከኢብራሂም ዑ. አ.

ከተጠቀሰው መቶ አመት በፊት የነበረውን የላብ–አደሩን ህዝብ ሁኔታ እንዳለ ትተነው ከተባለው ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ሁኔታ ብቻ ለማተት እንሞክራለን። ከቱርኮችና ከሚፋፊያዎቻቸው የመሳሪያና የሞራል ድጋፍ በማግኘት የአዳል ባላባት(ኤሚር) ማህፉዝ ደጋውን ኢትዮጵያ እ. ኤ. አ. ከ1501 አ. ም. አንስቶ መውረር በጀመረ ጊዜ ላብ-አደሩ ህዝብ አዲስና ከባድ ችግር ገጠመው። ይህ በውጭ ጠላቶች የሚደገፍ ዘግይቶ ወደ «ጂሃድ» የተለወጠው የጠረፈኞች ወረራ እስከ መቶ አመቱ አጋማሽ ድረስ በመንተቱ፤1ኛ. ገበሬው ስራውን ይቀጥል ዘንድ አስፈላጊ የሆነውን ፀጥታ ነሳው፤2ኛ. ንጉሰ ነገስቱና መኳንንቱ ወረራውን ለመመከት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ገበሬውና ከብት አርቢው ህዝብ መቻል ግድ ሆነበት፤3ኛ. የወራሪንና የተከላካይን ዘረፋ በመሰልቸት ላብ–አደሩ ህዝብ ትዳሩን እያፈረሰ ወደ የከተሞች መሸሽ ግድ ሆነበት።

ከወረራው በፊት የነበረውን ያገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ እንመልከት። በዚያን ዘመን(እንዳሁኑ) ዋናው የሀገሪቱ የሀብት ምንጭ ግብርናና ከብት ርቢ ነበር። ምንም እንኳ አታራቢ ግምት ለመስጠት የሚያስችል ምንም አይነት ስታቲስቲክ ባይኖርም አገሪቱ በልዩ ልዩ እህል አዝመራ በጣም ሀብታም የነበረች መሆኗ ይታወቃል(1)። በያለበት የስንዴና የገብስ፤የማሽላና የሽንብራ፤የምስርናየአተር፤የዳጉሳና የጤፍ ሰብልና ምርት፤እንዲሁም ብዙ አይነት ጐመንጐመኖች ይገኙ ነበር(2)። የእህሉ ጉተራ የነበረውን ይህንን ደጋውን ክፍል ወር ማስገበር ኢትዮጵያን በሙሉ ማስገበር መሆኑን ማህፉዝ የተገነዘበው ይመስላል። ይህም የሚታወቀው ሃያ–አምስት አመት ሙሉ ያለማቋረጥ ወረራውን በደጋው ላይ በመፈፀሙ ነው። ነገር ግን ደጋውን ለመያዝ ጥረቱን በሚቀጥልበት ጊዜ ገበሬውን ህዝብ ከባላባቱና ከወታደሩ ጋር አብሮ መጨፍጨፍ ከንቱ ስንዛሬ መሆኑን ስለተገነዘበው ገበሬውን የከባከብ ነበር።

ገበሬውን ማንከባከቡና ከአደጋ ማዳን መሞከሩ የረጅም ጊዜ ትሩፋቱን በመገመት ብቻ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያስከትለውን ጥቅም በመረዳት ነው። የወራሪው ሰራዊት ስንቁን የሚያገኘው የደገኛው ገበሬ ላብ ከሚያፈራው ምርት ነበር። ስለዚህ ገበሬውን ማጥቃት ራሱን መጉዳት መሆኑ ስለታወቀ ማህፉዝ ገበሬዎቹን በማረከ ጊዜ አይዟችሁ፤አትፍሩ፤ወደ የቤታችሁ በሰላም ጊዱ፤ለሚመጣው አመት እህል አምርታችሁ ቆዩኝ እያለ ያሰናብታቸው ነበር(3)።

የማህፉዝን ተስፋ ከትሬታ ጋር ያሙት ገበሬዎች በሃይማኖትና በፖለቲካ መናፍቅነት በየቦታቸው መናርን መረጡ። ይህን ያላመኑ ግን ስራቸውን ፈተው ቅርሳቸውን ጥተረው ወረራው ገና ወደአልደረሰበት ከተሞች ተሰደዱ። የወራሪውን ተስፋ ለማመን የማይቻል የሆነበት ምክንያት ማህፉዝ ገበሬውንና ሌላውንም ላብ-አደር ህዝብ የሚፈልገው ለሚያስገኝለት የኢኮኖሚ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለባርነትም ጭምር ነበር።

የባሪያ ነጋዴ አረቦች ከልዩ ልዩ የአፍሪካ አገሮች የሰው ልጆችን እየጠለፉ እንደ ሸቀጥ ወደ አረብ አገርና ወደ ፋርስ ወደ ህንድም በመሸጥ የሞቀ ንግድ አቋቁመው ነበር። በተሸጡበት ቦታ ሁሉ ኢትዮጵያውያኖች በወታደርነት ዝና አትርፈው ነበር። ይህን የሚያውቁ የአረብ መኳንንት የኢትዮጵያን ባሮች በጣም ይፈልጉ ነበር። ማህፉዝ ይህን ስለሚያውቅ ይልቁንም የአረቦችንና የቱርኮችን እርዳታ በበለጠ ለማግኘት በየጊዜው ብዙ ሰዎች እያፈሰ ወደ አረብ አገር በባርነት፤በገፀበረከትነት ያሻግር ነበር።

የእስላሞች ሃይል ባልደረሰበት አውራጃዎች የሚኖሩት ገበሬዎችም ኑሮ ከፍ ብለን ከተመለከትነው ምንም የተሻለ አልነበረም። የንጉሰ ነገስቱ ሰራዊት ከልክ ያለፈ ነበር። ንጉሰ ነገስቱን የሚያጅበው ሰራዊት በቅሎዎች ቁጥር አንድ መቶ ፲ ያህል እታ አግጋጊ አጋሰሶች ቁጥር ከዚህ ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ የሚበልጥ መሆኑን ስለምናውቅ(4) የፈረሰኛና እግረኛው ሰራዊት እንዲሁም የቤተ ሰብ ቁጥር ሲጨመር የእጀብ ብዛት ቅርብ ሚልዮን ነው ለማለት ይቻላል። በያውራጃው የሚገኙት መኳንንትና ባላባት አሽከርቻቸውን እያስከተሉ በየጊዜው

ከንጉሰ ነገስቱ ሰራዊት ይቀላቀሉ ነበር። እስላምን ለመሸሽ ከያውራጃው የሚሰደዱት ገበሬዎች ደግሞ ለየመኳንንቱ አሽከርነት (ማለት ወታደርነት) ይገቡ ነበር። ባጭሩ የንጉሰ ነገስቱ ዘላንነት ዘላን ሁብረ-ሰብን ፈጠረ። ቤተክርስቲያን፣ንግድና ኢንዱስትሪም(የጅ ጥበብ ሙያ) ዘላን ሆኑ።

የንጉሰ ነገስቱ ዘላንነትና የሰራዊት ብዛት የገበሬውንና የሌላውንም ላብ-አደር ኑሮ እያመነመነው ከመሄዱም ይልቅ የቀረውን ከመሬቱ ጋር ተቆራኝቶ የሚኖረውን ኑሮ በበሽታ አደኸየው። በሰላም የሚኖረው ገበሬ ለንጉሰ ነገስቱ ግብር፣ቅቤ፣ዘቀጭ፣ፈረስ፣ፍራሽ፣ልብስ በርካብቱ አማካይነት መገበር ያኔ ጀምሮ የነበረ ግዴታው ነበር። እንዲሁም ለጓላ ቡቱ የተጠየቀውን ያህል መገበርም የፀና ደንብ ነበር።

በ17ኛው መቶ አመት መጀመሪያ ኢትዮጵያን የጐበኘ አንድ ሚስዮናዊ እንዲህ ይላል፤«ወታደሮች አውራጃዎች ደግሞ ገበሬው ቀለብ እንዲሞን ስለሚገደድ ብዙ አሰባስ አይገባርም። እስርቤሰ የሚደንብረው እያንዳንዱ ገበሬ ለንጉሰ ቀለብ በጭፍራ፣ይህን ቀለብ 'የንጉሰ ቀለብ' ይሉታል። ይህ ለም መሬት የጐደፉን ትንሽነት ለማስገንዘብ ያህል ነው። ጭፍሩ ግን ወዚህ ለም የሚታወቀው ቀለብ አንድ ጭነት ጥሬ እህል ነው። እንግዲህ ብዙ ገበሬዎች ልላሉ በጠቅላላው የሚሰበሰበውን እህል መጠን ለመገመት ይቻላል...። ከዚህም በላይ መንግስት በየጊዜው በሚገምተው መጠን ለበልርስቶች ግብር መክፈል አለበቸው። ከግብሩ በላይ እያንዳንዱ ገበሬ ሁለት ጉዱ ማርና ሁለት ዶሮ(ለትንሳኤና ለመስቀል አመት በአሉች) መገበር አለበት(5)።»

ከዚህም በላይ የንጉሰ ነገስቱ ሰራዊት ከትሞ በሚሰፍርበት አውራጃዎች የሚገኙት ገበሬዎች ሁሉ ሰራዊቱን የመቀለብ አዲስ ግዴታ ተጣለባቸው። ገሬበዎችን በበለጠ ችግር ላይ የጣላቸው የአገሩንም የኢኮኖሚ ሀይል ሊያቆረቁዘው የቻለው በተለይ ይህ አዲስ ግዴታ ነበር። የሰራዊቱን ብዛትና አጥፊነቱንም መጠን የሚያስገነዝብ የአፄ ሰርፀ ድንግል ቃል ነው፤እንዲህ ይላል፤«ሰራዊታችን እጅግ ብዙ ስለሆነ እልፍ ሰፍርት ስለሌው በትገሬ ጥቂት ብቆይ ናር አገሩ አመድ ይሆን ነበር(6)።»

ንጉሰ ነገስቱን ያላጅብ በባላገር ተቀምጠው ርስታቸውን የሚያሳርሱ መኳንንቶች ወደ ዘመቻ እንዲሄዱ ይታዘዛሉ። ይህ ትእዛዝ

በመጣ ጊዜ ገበሬው ማናቸውንም ስራውን አራግፎ እንዲከተል ይታዘዛል። በሁለት ወይም በሶስት ቀን ውስጥ አንድ መቶ ሺህ ሰው ድረስ በክተት የተዘጋጀበትም ጊዜ አለ። እንግዲህ ይህ ሁሉ ሰራዊት የመኳንንቱ ጭፍራ ሆና ትዳሩን አዳፍና ሲዘምት ወጪውን የሚችል ራሱ ነበር። ከቤቱ ሲወጣ የበሶና የማሽላ ዳቦ ስንቁን ይዞ ይወጣል። በዘመቻ ላይ ባለበት ጊዜ ስንቅ ካለቀበት የሌሎቹን ሰላማዊ ገበሬዎች ከብትና እህል እየዘረፈ እንዲበላ ይፈቀድለታል። ይህንንም ለማድረግ የሚደፍረው ወታደርን አስተናግዱ የሚል ህግ ስለነበረ ነው። ይህን ህግ የማያከብር ገበሬ ወይም ቤተሰብ በጥብቅ ይጠበቅ ነበር። ወታደሩ በምግብ ብቻ አይመለስም ነበር። ባንድ መንደር የሰፈረ ጊዜ ያቺ መንደር አመድ ትሆናለች። እያንዳንዱ ወታደር በየገበሬው ቤት እየገባ ቢሻው ይዳበላል፤ቢሻውም ባለቤቱን አስወጥቶ ራሱ ዋና ሆና ይቀመጣል። ጌልዋ የዘመተ ወይም የሞተባት ሴት ቤቷና ምግብዋ ብቻ ሳይሆን እሷም ትደፈራለች።

እንግዲህ ይህ በህግ የተፈቀደ ዘረፋ በያለበት በሰፈው ስለተነሳ ተዘርፈው የደኸዩ ገበሬዎች ደግሞ ሌላውን ገበሬ ለመዝረፍ የመኳንንቱ ጭፍሮች እየሆኑ ይዘምቱ ነበር።

በቤተ መንግስቱና በሰራተኛው ገበሬ መካከል የነበረው መራራቅ በጣም የላቀ ነበር። ምንም እንኳ ቤተ መንግስቱ ዘላን ቢሆንም ምኞት ያልጉደለው መሆኑን ተረድተናል። በሚከትምበት ቦታዎች ሁሉ ማናቸውም ስነስርአት አይጉድልም ነበር። እንዲያውም በቤተ መንግስቱ ከተማየነበረው አኗኗር በጣም የሚያስደንቅ ነበር። ንጉሰ ነገስቱን የሚያጅብ ብዙ ሰረዊት ነበር ብለናል። ይህን ሰራዊትና ስራ ፈት ደጅ የሚጠናውን መኳንንት ሁሉ የሚያዝናኑ ብዙ የመጠጥ ቤቶችና ኮማሪቶች ይገኙ ነበር። ዘመኑ በሚፈቅደው ጌጥ የሚሽቀረቀሩ በጊና፣በኩል በንቅሳት የቆነጁ በብዙ አእላፋት የሚቆጠሩ ኮማሪቶች ይገኙ ነበር። ባጭሩ የንጉሰ ነገስቱ ከተማ ለብዙዎች የመፈንጫ ከተማ ሲሆን የባላገሩ ኑሮ ግን ሲኦል ነበር።

የባላገሩ ህዝብ ከከተመኛው እጅግ የራቀ ሁብረ-ሰባዊ ክፍል ነበር። ይህ ክፍል «ባለጌ» ይባል ነበር። «ባለጌ» ማለት በባላገር የሚኖር ላብ-አደር ገበሬ ወይም ‹ፔዛንት ክላስ›ማለት ነው። ይህ መጠሪያ የሁብረ-

ሰብ መለዮ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚም መለዮ ይመስላል። ስለዚህ «ባለጌ» በሚለው ቃል የሚጠሩ በጣም የደኸዩ፣ ላብ-አደር ገበሬዎች ናቸው። ለምሳሌ በአልባሳና በእቃ እጅግ የደኸየ ቤተክርስቲያን በዘልማድ «የባለጌ ቤተክርስቲያን» ይባል ነበር። በየጊዜው የሚዘርፍዋቸው የእስላምና የንጉሰ ነገስቱ ሰራዊት ገበሬውን በችግር ላይ የጣሉት መሆናቸውን ተረድተናል። የገበሬውን መዘረፍ በጣም ያጠናበት በንጉሰ ነገስቱ ትእዛዝ ፀጥታ ለመጠበቅ በየውራጃው ተሰማርተው እንዲኖሩ የታዘዙ «ጪዋ» የተባሉ ሰራዊቶች ናቸው። «ጪዋ» ማለት ወታደርነትን ሙሉ ሙያ አድርጉ ሁል ጊዜ በትጥቅ ይገኝ የነበር የባለገሩን ፀጥታ የሚጠብቅ ወታደር ነው። ጪዋዎች አፀላቸውን የሚያገኙት በሰላም ጊዜ ገበሬውን በማስገበር፣ በጦርነት ጊዜ ከብትና እህል በመዝረፍ ነበር። በሁለቱ ህብረ ሰባዊ ክፍሎች፣ ማለት በጪዋና በባለጌ መካከል ስምምነት አልነበረም። ጪዋና ባለጌ የሚሉት ቃሎች በዚያን ጊዜ እንኳን የሞራል ትርጉም ነበራቸው። ይልቁንም የእስላም ወረራ በየጊዜው እያየለ ስለሄደ ጪዋዎቹ እንኳን ስ የገበሬውን ፀጥታ ሊጠብቁ ቀርቶ የራሳቸውንም ደህንነት መጠበቅ ስላቃታቸው ለገበሬው ተጨማሪ ሸክም መሆናቸው ግልፅ ነው።

የንጉሰ ነገስቱ ከዜጎቹ መራቅ በየውራጃዎቹም የባላባቱና የጪዋዎቹ ሀይል እየጠነከረ መሄድ ያገሩን ህግና ስርአት በጣም አደከመው። ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ብዙዎቹ ገበሬዎች እየተንጋጉ ለመኳንንት አሽከርነት (ጭፍራነት) ገቡ። ሌሎቹም በየመንገዱ እያደፈጡ ነጋዴውንና መንገደኛውን እየነጠቁ መኖርን መረጡ።

ማህፉዝ ከሞተ በኋላ አግቹ መሀመድ ግራኝ ተከተለ። ከ1527 ጀምሮ እስከሞተበት እ.ኤ.አ. 1542 ድረስ ኢትዮጵያን በሙሉ ወር መግዛቱ ማንም ያውቀዋል። ነገር ግን በዚህ ላይ ለማተት የምንሞክረው በላብ-አደሩ ህዝብ ላይ ያስከተለውን ጉዳት ነው። ግራኝ የተነሳው በወታደራዊ ትጥቅ ብቻ ሳይሆን በአይዶሎጂም ረገድ ተዘጋጅቶ ነበር። የሱ ሁሳብ የወረራቸውን አውራጃዎች እስልምና በአላህ አንድ አድርጉና አስታርቆ ለማስተዳደር ይመስላል። የንጉሰ ነገስቱ ሰልጣን እምብዛም ባልደረሰባቸው አውራጃዎች ለምሳሌ በባሌ፣ በሲዳሞ የሚኖሩ ሁሉ የግራኝን ወረራ በደስታ ተቀበሉት። በየደጋው የሚገኙት ገበሬዎች ግን ሳይ

ሳይወዱ የግራኝን ሃይማኖትና ገዥነት ተቀበሉ። ይህ የመንፈስ አንድነት ከመፈጀት ያድናቸው እንጂ በወረራው ጊዜ ከመዘረፍና ሀብታቸውን ከመነጠቅ አላዳናቸውም። ግራኝ ወረራውን በጀመረበት ጊዜ አብረውት የዘመቱ የዶንከሌና የሱማሌ እንዲሁም የሌሎች ነገዶች ወታደሮች ደገኛውን ላብ-አደር ገበሬ መዝረፍ እየያዙም በባርነት መሸጥ ጀምረው ነበር። ይህም አድራጐት ያለስጋት ከስራ ለመዋል የሚያስችለውን መሰረታዊ ፀጥታ ስለነሳቸው ብዙዎች ገበሬዎች ነፍሳቸውን ለማዳን እየተሳደዱ ወደ ሌሎች ቦታዎች ሄዱ።

ነገር ግን የግራኝን ወረራ እርግጠኛ ጅሃድነት ከተገነዘቡት በኋላ ወታደሮቹ በዲሲፕሊን መሪያቸውን ይታዘዙ ጀመር። ከዚህ በኋላ ዘረፋውን ችላ አሉት፣ ገበሬውንና እረኛውን ማሳደዳቸውን ትተው የንጉሰ ነገስቱን ሰራዊት ማሳደድና አብያተ-ክርስቲያናትን ማቃጠል ጀመሩ። የወረራውን አያልነት የተረዱ ከንጉሰ ነገስቱ እየከዱ ለግራኝ ገቡ። ያ በሚልዮን ይቆጠር የነበረው የንጉሰ ነገስቱ አጀብ ተበተነ። የዘመኑ ንጉስ አጼ ልብነድንግል ራሳቸውን ለማዳን ከቦታ ወደቦታ ሲንከራተቱ ነበር።

ሰራተኛው ህዝብ የግራኝን ፈጣን ድል ተቀብሎም ሰላም እየገበረ ለመኖር የመረጠበት ምክንያት ዋራሉ ስለሞተ ነው የሚሉ አሉ(7)። ይህን አስተያየት ለመቀበል አስቸጋሪ ነው። ህዝቡ ይህን እርምጃ ለመውሰድ ያበቃው፣ ሰርቶ ለመኖር ትዳሩም ተከብሮለት ለመኖር የሚያበቃውን ህግና ስርአት ለማስከበር የሚችል ሀይለኛ መንግስት የተቋቋመ መሆኑን ስለተረዳው ይመስላል።

ከዚያ በፊት በአገሩ በሙሉ ህግና ስርአት እየጠፋ በመሄዱ ብዙ ላብ-አደር መንደረተኞች ቤታቸው ንብረታቸው ትዳራቸው መደፈሩን አይተናል። በዚያን ጊዜ ቤተክህነት ራሷን ለማዳን የምትጣጣርበት ጊዜ ስለነበር የምእመናኑን ክርስትና የምታጠነክርበት የሞራል ሀይል አልነበራትም። ቤተክርስቲያን የንፅህናን ኑሮ ዲሲፕሊን አስከባሪት ሀይል በማጣቷ ህዝቡ ኢክርስትና የሆነ ኑሮ ይኖር ነበር። አለቃ ታዬ እንዲህ ይላል፣ «አርን የወንድሙን ሚስት አገባ ስል ከላይ የጠቀስኩትን የሚያነብ እምብዛም ግድነት አይገባውም፣ ምክንያቱም በአገሩ ባህል መሰረት ወንድም የወንድሙን ሚስት ቢደፍር እንደ ነውር የሚቆጠር አ

ይደለም(8)።

አፄ ልብነ ድንግል እ.ኤ.አ.1540 ሞቱ። ገሬኛም ከሁለት አመት በኋላ በጦርነት ላይ ተመቶ ሞተ። ከሱም ሞት በኋላ የእስላም ወረራ እየቀለለ ሄደ። በአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግስት ደግሞ ከሀረር በስተቀር መላው ኢትዮጵያ ከእስላም አገዛዝ ነፃ ሆነ። ሀረርም እ.ኤ.አ.በ1575 ወደቀች። የእስላም ወረራ እየቀለ ለመሄድ ሲጀምር ንጉሰ ነገስቱ በየአውራጃው እየሄደ ከግራኝ ግዛት ነፃ በወጡት አውራጃዎች ሁሉ የጥንቱን ስርአት እንደገና ይመሰርት ጀመር። ለምሳሌ አፄ ሰርፀ ድንግል ባላባቱን በሀይል ወይም በማግባባት ወደ ክርስትና በመለወጥ የፊአዳል መሬትነታቸውንም በህግ አፀደቀላቸው(9)። ባንዳንድ አውራጃዎችም ለምሳሌ በዳሞትና በባሌ ገበሬውን ህዝብ እያስገበሩ የሚኖሩ ብዙዎች ደገኞች ክርስቲያኖች ተመሩ።

የቀድሞውን ስርአት ወይም የባላባት አገዛዝን ስርአት ባዲስ የመመስረቱ እቅድ የታሰበውን ዉጤት ከማስከተሉ በፊት የኦሮሞዎች መምጣት ባጭር አስቀረው። ኦሮሞዎች ከመቶ አመቱ መካከል ጀምረው ከሱማሌ ድንበር ከሚገኘው ከቀድሞው መኖሪያቸው ወደ ምእራብ በመግፋት በመላ ኢትዮጵያ ተሰራጩ። የኦሮሞዎች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት አዲስ የታሪክ ምእራፍ ጀመረ። ህብረሰባዊ ድርጅታቸው በዲሞክራሲና በጋርዮሽ ኑሮ የተመሰረተ ስለነበር ባቋኟቸው ቦታዎች ሁሉ የራሳቸውን የዲሞክራሲ አስተዳደር መሰረቱ። «ጋዳ» የሚባለው ድርጅት አባል የሆነ ሰው ሁሉ የጋዳውን መሬት እያረሰ የጉልበቱን ፍሬ የራሱ መጠቀሚያ ያደርግ ነበር እንጂ ለጪቃ፣ለበላባት፣ለንጉሰ አይገብርም ነበር።

የሆነው ሆኖ አሁን በምናጠናው 16ኛው መቶ አመት የኦሮሞዎች ወደ መካከል ኢትዮጵያ መምጣት ገና በመጀመር ላይ ስለነበር በህብረ-ሰቡና በፖለቲካ ረገድ የቀድሞውን ደገኛውን ክርስቲያናዊ አገዛዝ የቱን ያህል እንደለወጠው ለመረዳት አይቻልም።

የኦሮሞዎች መፍለስ በደቡብ ክፍለ አህጉር ይገኝ የነበረውን ላብ-አደር ህዝብ ውደ እጥፍ ገባሬ ለመለወጥ(ማለት ባንድ በኩል ለራሱ ባላባትና በሌላ በኩል ለንጉሰ ነገስቱና አገር አቅኚዎች)መጀመሪያ አፄ ገላውዴዎስ ቀጥሎም አፄ ሚናስና ሰርፀ ድንግል ያቀዱትን ባጭሩ

ስለቀጨው ነው። በዚህ ፅሁፍ ላይ ከፍተኛ ግምት በመስጠት የጠቀስነው። ከሀረር መውደቅ ጀምር እስከ መቶ አመቱ መጨረሻ ድረስ ያለው ጊዜ በሙሉ የኦሮሞዎች ወረራና መፍለስ ጊዜ ስለሆነ ስለ ኢትዮጵያ ላብ-አደር ህዝብ የሰነዘርነውን ትንተና ከዚህ ላይ አቁመን አጭር ትችታችንን እናስከትላለን።

ይህ የተመለከትነው ጊዜ«የኢትዮጵያ ታሪክ» አንድ ክፍል ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት ትርጉም ምንድነው? ከነገስታቱ ዜና መዋዕልና ከንዳንድ መንገደኞች ፅሁፎች መረጃ በመታረም በፃፉት ባንዳንድ ልወደድ ባይ ታሪክ ፀሀፊዎች አገግመት የኢትዮጵያ ታሪክ የኦርቶዶክስ ክርስትናን ወግ ለመጠበቅ እንዲሁም ያንዲት አገር ነፃነትንም ለማስከበር በነገስታት የተደረገ የጀግንነትና የመስዋእትነት ታሪክ ነው። ለሌሎች ደግሞ ምስጢር የሌለው የነገስታት ገድልና ዜና መዋእል ነው።

በእውነቱ ከሆነስ የተመለከትነው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ የላብ-አደሩ የጀግንነትና የመስዋእትነት፣የጥቃትና የጭቆና ታሪክ ነው። «በኢትዮጵያ ታሪክ አፄ ወልደግርያም ቢነገስ አፄ ገብረግርያም፣የህዝብ እድል ሁል ጊዜ ጭቆና መከራ ሆና ቀርቷል(10)»ሲል አንድ ሰው ፅፏል። ላብ-አደሩ ህዝብ ለንጉሰ ነገስቱ፣ለመኳንንቱ እንዲሁም ለጪዋዎች ይገብር ዘንድ የሚገደድ ከመሆኑ በላይ በየጊዜው እየመጡ የሚቀሙትን ፋናዎችንም ችሎ የተቀመጠ መሆኑን አይተናል። የጭቆናው ማስፈፀሚያ መሳሪያም ቤተ መንግስትና ቤተ ክርስቲያን ነበሩ። መኳንንቱ ከነጪዋዎቻቸው በየአውራጃዎቹ‹ፀጥታን እንዲጠብቁ›ስልጣን ሰጥቶ የሚልካቸው ንጉሰ ነገስቱ ነበር። ላብ-አደሩን መንደረተኛ እየዘረፉና እያዋረዱ የሚኖሩትን እነዚህን የንጉሱን አሽከሮች «በእንግድነት» መቀበል የአምላክን ትእዛዝ መፈፀም ማለት ነው እያለች የምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ነበረች።

የዚህ መቶ አመት የኢትዮጵያ ታሪክ በእውነትም የላብ-አደሩ ህዝብ ፍዳ ነበር። እስላሞች ደገኛውን ህዝብ እንዲወሩ ያነሳሳቸው የጂሃድ መንፈስ ብቻ ሳይሆን የላብ-አደሩ ህዝብ ያስገኘውን ፍሬ እየዘረፉ ለመውሰድ ህዝብንም እየያዙ በባርነት በመሸጥ ሊያገኙ የሚችሉትም የኢኮኖሚ ጥቅም ጭምር ነበር። እንዲሁም ንጉሰ ነገስቱና መኳንንት

ቱ በያለበት የሚዘምቱት እስላሞች ተቅማቸውን እንዳይሸምቁችው ለመከላከል፤ላብ-አደሩ በበለጠ እንዲገብር የሚያስገድደውን ፊውዳላዊ አቋም ለማጠንከር ነበር እንጂ ያገርን ነፃነትና የኦርቶዶክስን ክርስትና፣ወግና ስልጣኔ ለመጠበቅስ ብቻ አልነበረም። ነገስታቱ ለኦርቶዶክሳዊት ክርስትና የነበራቸው እምነት ከንገት በላይ መሆኑን ወደፊት በምናቀርበው አምድ ላይ ለማስረዳት እንሞክራለን።

ይህ መቶ አመት የላብ-አደሩ ህዝብ የፍዳ ዘመን ነበር ያልንበት የጥረቱን ፍሬ ለመቀማት ሁለት ተቀናቃኞች በመጨፋጨፋቸው አንዱ አሸንፎ አገሩን መምራት እስተቻለ ድረስ የሁለቱንም ወገን ዘረፋ እንዲችል ስለተገደደ ነው።የዚህ መቶ አመት አውራ አርእስት የግራኝ ጦርነት ነበር። ታዲያስ የግራኝ ጦርነት አላማው ባላባቱንና መኳንንቱን ንጉሱ ነገስቱንም አጥፍቶ አገሩን እስልም ለማስገበር አልነበረም? ግራኝ ቢያሸንፍ ወይም ቢሸነፍ የኢትዮጵያ ላብ-አደር ህዝብ ከባርነት እንደማይወጣ ስለተገዘበውና የሁለት ጦር ዘረፋ ስላደከመው የጦርነቱን መፈፀሚያ ጊዜ ብቻ በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር።

«ሶስት ሺህ አመት» የነፃነት ዘመን የሚባለውን ታላቅ ኩምክና የማያውቅ የለም። የማን ነፃነት ነው ሳስት ሺህ አመት ሙሉ የተከበረ?የላብ-አደሩ ህዝብ ነፃነት አልነበረም፤በፍፁም። እርግጥ ነው የሶስት ሺህ አመት ነፃነት ነበር።ነገር ግን ይህ ነፃነት አንዱ ህብረሰባዊ ክፍል ሌላውን እያስገበረ የመግዛት ነፃነት ነበረ። በሃያኛው መቶ አመት የሚገኘው ላብ-አደር ህዝብም ሁኔታ ከተመለከትነው ከ16ኛው መቶ አመት ሁኔታ በምንም ረገድ አይሻልም። ይህን ለማተት የዚህ አምድ የጊዜ ወሰን ስለማይፈቅድ ለወደፊት በምንፅፋቸው አምዶች በሰፊው ለማተት እንሞክራለን።

የማመሳከሪያ ምንጮች፣

1. አልቫሬዝ፣ «ኢትዮጵያ ፖርቱጋዞች እንዳዩዋት» ምእ. 19 የዞረ)
2. በተጠቀሰው መፅሀፍ ምእ.47
3. ምእ.114 ገፅ 300-301
4. ምእ.88
5. Pais Péro፡História da Etiòpia,vol.I,ch.xxx. pp237-238
6. Pankhurst, Richard:An Introduction to the Economic History of EthioPia p.175
7. Trimingham,Spencer፡Islam in Ethiopia p.90
8. አልቫሬዝ፣«ኢትዮጵያ ፖርቱጋዞች እንዳዩዋት›ምእ.21 ገፅ 47
9. SaPelli,Luca Dei፡ Storia di Abbissinia,Vol.II,ch. XV,p.237
10. ‹ታጠቅ› ታህሳስ 1959 ገፅ 13

የቬየትናም ህዝብ ጦርነትና የምናገኘው ትምህርት

በዚህ አርእስት ስር ወንድም ፋና ያበረከተው ፅሁፍ ከተደረሰ ትንሽ ጊዜ አልፏል።ጊዜ ከማጠሩና ቦታ ከማነሱ የተነሳ ቀደም ብለን ለማውጣት ባለመቻላችን የተሰማንን ቅሬታ ስንገልፅ አሁንም ቢሆን የወንድም ፋና ድርሰት ያዘለው ትምህርት በጣም ጠቃሚና ጊዜ ያላለፈበት መሆኑን ለአንባቢዎች እያሳሰብን ነው።

ፅሁፉ ከተደረሰ ወዲህ (1ኛ) የሰሜንና የደቡብ ቬየትናም ህዝቦች በየጊዜው ከገኙት ድል የተነሳ የያንኪ ኢምፔሪያሊዝም በሰሜን ቬየትናም ላይ ያወርድ የነበረውን የቦምብ ናዳ እንዲያቆም ተገዷል፤ (2ኛ) ከአንዳንድ እንደ ደሴት ከሚቆጠሩ የጠላት ጦር ሰፈሮች በቅተ

ቀር የቬየትናም ነፃ አውጪ ግንባር አገሩን በሙሉ ነፃ አውጥቶአል፤ (3ኛ) የፓሪሱ የሰላም ውይይት ተጀምሯል፤(4ኛ) የደቡብ ቬየትናም ጊዜያዊ መንግስት ተቋቁሞአል።

አሜሪካን ያለመውን ድል በጦር ሜዳ ላይ ማግኘት ባቃተው ጊዜ ግብዣዊ የሰላም ፍለጋውን ማውራት ጀመረ። ይኸው የሰላም ውይይት ከተጀመረ ከአመት በላይ ሆናታል። እስካሁን አሜሪካኖች አንድም ለጉዳዩ መፍትሄ የሚሆን አቋም አላቀረቡም፤ ዳሩ ግን እየጉብጉቡ ከቁም ነገሩ ለመሸሸ «ስለ ወሬ ወሬ ሲያወሩ» ጊዜ ማሳለፋቸው አታላይ የሆነ ሰበካቸውን በገሀድ አጋልጦታል። ውይይቱም ከተጀመረ ወዲህ የጦር ሀይላቸውን እያጠነከሩና በህዝቡ ላይ የሚፈፅሙትን ስቃይ እያባሱት ሄደዋል።

የቬየትናም ነፃነት ግንባር በሰላም ውይይቱ ገበታ ላይ ደጋግሞ ያቀረባቸውና የሚያቀርባቸው መፍትሄዎች ልክ እንደጦሩ ሜዳ ስትራቴጂው ቁም ነገር ያላቸውና ከልብ የሚፈልቁ መሆናቸውን (1) ኖቬምበር 3፤1968 ባወጣው መግለጫ ውስጥ የሰነዘራቸው አምስት ነጥቦች (2) ሜይ 8፤1969 በፓሪስ የሰላም ሸንጎ ላይ ያቀረባቸው አስር ነጥቦች በግልፅ ይመሰክራሉ።

አሜሪካኖች ፀረ-ሬቮሉሽናዊ በሆነ በሁለት ታክቲካቸው አንድ በኩል ስለ ሰላም በመናገር፤ በሌላ በኩል ወንጀላቸውን በማባባስ ድልን የሚያገኙ መስሏቸው ይሆናል! ነገር ግን ይህን አታላይነት የቬየትናም ተዋጊዎች በሚገባ ተረድተውታል። በጦር ሜዳ ላይ ሆነ በውይይት ገበታ ላይ የቬየትናም ህዝብ ሙሉ ድልን ሳያገኝ እርፍ እንደማይል ደጋግሞ ተናግሯል።

በቅርቡ የተቋቋመው ጊዜያዊው የደቡብ ቬየትናም ህዝብ መንግስት የዚህ ምስክር ነው። አንዳንድ የምእራብ ሰባኪዎች እንደሚያወሩት ለፐርፓጋንዳ የተሰነዘረ መሳሪያ አይደለም። ቀስ በቀስ እያደገ የመጣና ከህዝብ የፈለቀ፤በጠቅላላው ህዝብ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ህዝባዊ መንግስት ነው። የቬየትናምንም ህዝብ እስካሁን ባሳየው የተራቀቀ የአመራር ዘዴ አራምዶ ወደ ሙሉ ነፃነት እንደሚያደርሰው አይጠረጠርም።

ከቬየትናም ጦርነት ምን ትምህርት እናገኛለን።

ክፍል(1)

1. መግቢያ

የቬየትናም ህዝብ ለብሄራዊ ነፃነቱ መዋጋት ከጀመረ ብዙ ጊዜ ሆናታል። የሃያኛው ክፍለ ዘመን ከተከፈተ ጀምሮ መብቱንና ባህሉን ለመጠበቅ በጦር ሜዳ ተሰልፎ፤ አንዴ የጃፓንን ኢምፔሪያሊዝም አንዴ ደግሞ የፈረንሳይን ተዋግቶ አሸንፏል። ዛሬ ደግሞ አለም-አቀፍ (ኢንተርናሺናል) የሆነውን፤በጦር ሀይል እጅግ የላቀውን የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም በመውጋት ላይ ይገኛል። ምንም እንኳ አሜሪካ በጦር ሀይል የደረጀ ቢሆንም ድሉን እያጣና እየተሸነፈ ለመሄዱ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። በቬየትናም የአሜሪካንን ጦር ሲመሩ የነበሩት የማክናማራና የጄኔራል ዌስትሞርላንድ መሻር ለምሳሌ፤የቬየትናም ህዝብ ኢምፔሪያሊዝምን ማጥቃቱን ይገልፃል።

የቬየትናም ህዝብ የሚዋጋው ለራሱ ነፃነት ብቻ አይደለም ለተጨቆነውና ለተዘረፈው ለአለም ህዝብ በተለይም ለ«ሶስተኛው አለም»(እስያ፤አፍሪካ፤ደቡብ አሜሪካ) ህዝብ ነው። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አለም-አቀፍ ነውና።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚዘርፈውና የሚጨቁነው የአለምን ህዝብ በሙላ ነው። ስለዚህ ኢምፔሪያልዝምን መውጋት፤ማጥቃትና ማኮሰስል ወይም አላማውን ማጨናገፍ፤ ሀይሉ እንዲደክም፤ ዝርፊያውና ጭቆናው እንዲቀነስ ያደርጋል። ይህንን በመረዳት የኪውባው መሪ ካስትሮ«የቬየትናም ህዝብ የሚዋጋው ለኛም ጭምር ነው» ብሎ ያለው በጣሙን እውነት ነው። ኢምፔሪያሊዝም ሲደክም የቦሊቪያም ህዝብ ሆነ የኢትዮጵያ፤ የላኦስም ሆነ የጋና ህዝብ ነፃነቱን ለማግኘትና ከጭቆና ቀንበር ለመውጣት ታላቅ እድል ይኖረዋል። የአሜሪካን መሪም

(1) ፋና ባሜሪካን የሚገኝ ያንድ ተማሪ የብርእ ስም ነው።

ች።ቪየትናም ከመለጠን ደቡብ ምስራቅ እስያ፤ከዚያም መላው እስያ ከጃችን ያፈተልካል»ብለው የሚሰጉት የገብራቸውን ውስጠ-ምስጢር አውቀውት ነው።

የቪየትናም ህዝብ ሀይለኛ የሆነውን ኢምፔሪያሊዝም በምን ዘዴ ለማገታት ቻለ? በመሳሪያ ሀይል፤በወታደር ብዛትና በሀብት ልማት ቪየትናም እንደ ትንኝ፤አሜሪካ እንደ ዝሆን ናቸው።ይሁን እንጂ የቪየትናም ተዋጊዎች በብሄራዊ የነፃነት ግንባራቸው(የብ.ነ.ግ.) ተመርተው የአሜሪካንን የምድርና የአየር ጦር ሲያንገላቱና ሲሰባብሩ ይታያሉ።በኢያንድራንግ፤በዳክቶ፤በኮንቲየን፤በዳናንግና በቅርብም በመላው ቪየትናም ወራሪውን ጠላት ጦር ገጠመው ሀይሉን ገነጣጥለዋል።ከዚህም አልፈው የጠላታቸውን ወታደሮች በኬሳን ላይ ሳይወዱ እንዲሰበሰቡ አድርገው ከከበብዋቸው በኋላ የዲየን ቢየን ፉን የመሰለ ውርደት ሊያከናንብዋቸው ተሰናድተዋል።

የዚህ ሁሉ ምስጢሩ ምንድነው?የቪየትናም ህዝብ በምን ዘዴ በምን መሪ ሀሳብ ነው እስከዚህ ሊያይል የቻለው? በሀብትና በቴክኖሎጂ ያልደረጀችው ቪየትናም ሀይለኛ የተባለውን አሜሪካን እንዴት አድርጋ ልትቋቋመው ቻለች? እኛ ወደፊት በአሜሪካን የተደገፈውን የኢትዮጵያን የፊውዳል አገዛዝ ለመቋቋም ያቀድነው ነ ቪየትናም ህዝብ ትግል ምን ትምህርት እናገኛለን?

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመርመር መጀመሪያ የቪየትናምን ጦርነት ታሪክ መመልከት ያሻናል። የትግሉን ታሪክ በትክክለኛው ከል ተረዳነው ጠቃሚ ትምህርት ልናገኝበት እንችልም።እንዲያው ከግድንቅ ከመገረም፤ቪየትናሞች ጉብዞች ናቸው ከማለት ሌላ የጦርነቱን ውስጠ-ምስጢር፤የኢምፔሪያሊዝምን ተንኮል፤በጠቅላላው የሬቮሉሽናዊ ትግልን መሰረተ-ደንብ ጠልቀን ለማወቅ እንችልም። በዚህ ምክንያት ይህ ድርሰት መጀመሪያ የጦርነቱን አነሳስና የትግሉን ታሪክ ባጭሩ ይተነትናል። ከዚያ በኋላ ወደ መጨረሻው የቪየትናምን ህዝብ አላማና የትግላቸውን መልክ በመመርመር የሀገራችን የነፃነት ተዋጊዎች ምን ጠቃሚ ትምህርት ለማገኘት እንደሚችሉ ይገልፃል።

2. የቪየትናም ጦርነት አጭር ታሪክ

ብዙ ሀተታ እንዳይበዛ ይህ ድርሰት ተደቡብ ቪየትናም ስለሚደረገው ጦርነት፤ማለት ከ1954 እ.ም. (2) በኋላ ስለተጀመረው ትግል ብቻ እንጂ ከዚያ በፊት ስለሆነው ታሪክ አይጠቅስም።ይሀንንም ስል የቪየትናም ህዝብ ከፈረንሳይ የቅኝ ግዛት ለመውጣት ያደረገው ውጊያና አሁን የሚያደርገው ውጊያ የተለያየ ነው ማለቴ አይደለም።የቀድሞው የነፃነት ትግል ዲየን ቢየን ፉን ላይ አላለቀም። ፈረንሳይ ሲሸነፍ አሜሪካን ተተክቶ ትግሉ አሁንም እንደቀጠለ ነው። የጠላቱ ስም ተለወጠ እንጅ የትግሉ አላማና አይነት አሁንም አልተለወጠም። ታሪኩን ከ1954 መጀመሬ ድርሰቱ አለቅጥ እንዳይረዝም ነው እንጂ ከ1954በፊትና በኋላ የተደረጉት ውጊያዎች በአላማቸው የተለያዩ አይደሉም።

የፈረንሳይ መንግስት ቪየትናምን በፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ውስጥ ለማስቀረት ብዙ አመታት ከተዋጋ በኋላ በ1954 እ.ም.በዲየንቢየንፉ ላይ የመረረ ሽንፈት ስለወደቀበት መሸነፉን አምኖ ቪየትናምን ለቆ ለመውጣት ቁርጥ ሀሳብ አደረገ።ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ የነበሩት የአሜሪካ መሪዎች ውጊያውን እንዲቀጥል ቢገፋፉትም የፈረንሳይ መንግስት ለመዋጋት አቅም ስላነሰው መታረቅ ፈለገ።የአሜሪካን መንግስት ፈረንሳይ በጦርነቱ ለሚያደርገው ወጪ ከመቶ ሰማኒያውን ይከፍል ስለነበር፤ ፈረንሳይ ስለተሸነፈና ጦርነቱን አልቀጥልም ስላለ ተመርሮ ቂም ይዞ ነበር።በዚህ ምክንያት በ1954 እ.ም. የጄኔቫን ውል ሲፈራረሙ አሜሪካን አልፈርምም ብሎ ከሌሎች ተነጠለ። አልፈርምም ይበል እንጂ ውሉን እንዳያፈርስ ቃል ገብቶ ነበር።

የጄኔቫው ውል ከሰፈራቸው የስምምነት ገጹታዎች ዋናዎቹ ሳስት ናቸው፡-

— 1ኛ. ፈረንሳይ ቪየትናምን ለቆ እስኪወጣ ድረስ የጦር ሀይሉን ከሰሜን ቪየትናም ወደ ደቡብ እንዲያዛውርና የቪየትናም የነፃነት ተዋጊዎች ወደ ሰሜን ለመዛወር እንዲችሉ። ይህ መዛወር እንዲቀና ቪየትና

(2)በዚህ ድርሰት ውስጥ የተጠቀሱት እ.ም.እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ነው።

ም ለጥቂት ጊዜ ለሁለት ተከፍላ የፈረንሳይ ጦር በደቡብ እንዲሰፍር። ቬየትናም የተከፈለችው ለጥቂት ጊዜ እንጂ ለዘላለም አልነበረም።

— 2ኛ. ከሁለት አመት በኋላ(ማለት በ1956እ.ም.) ጠቅላላ ምርጫ ተደርጎ፤ሰሜንና ደቡብ ቬየትናም አንድ ሆነው በአንድ መንግስት እንዲተዳደሩ ህዝቡ በምርጫው እንዲያፀናው።

— 3ኛ. በሰሜንም ሆነ በደቡብ ማንኛውም የውጭ አገር ጦር፤የጦር መሳሪያ ወይም ለጦርነት የሚሆኑ እቃዎች እንዳይገቡ።

የጀኔቫ ውል ተፈርሞ ቀለሙ ሳይደርቅ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ስምምነቱን ማፍረስ ጀመረ። ደቡብ ቬየትናምን በጁ ለማስገባት ዲየም የሚባል አሻንጉሊት በጠቅላይ ሚንስቴርነት እንዲሾም አድርጎ በርዳታ ስም ጦርና መሳሪያ ማስገባት ጀመረ። በ1954 መጨረሻ አሜሪካ በቬየትናም ውስጥ የጦር ሚስዮን አቋመ።በ1955እ.ም. ማ.ገ. (MAAG) የሚባል የጦር ድርጅት ልኮ የደቡብ ቬየትናምን የጦር ሀይል ለማሰልጠን ተነሳ።ያሜሪካን መንግስት እንደገለፀው ከ1954-1962 2.4ቢሊዮን ብር በኢኮኖሚና በጦር እርዳታ መልክ ለዲየም መንግስት ሰጥቷል።የአሜሪካን የጦር ፅህፈት ቤት ስለአሜሪካን ወታደሮች ቬየትናም መግባት የሚከተለውን ማስረጃ ሰጥቷል፤

1954-1959 650 ወታደሮች(የያመቱ አቬሬጅ)

በ1960 መጨረሻ	850	በ1963 መጨረሻ	16,300
በ1961	3,200	በ1964	23,300
በ1962	11,300	በ1965	184,300

ዛሬ ያሜሪካን ወታደሮች ከግማሽ ሚልዮን በላይ ናቸው። የሳይጎን አሻንጉሊት መንግስት ወታደሮችና የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አባሪ መንግስታት (እንደ ደቡብ ኮሪያና አውስትራሊያ)ወታደሮች ሲጨመሩ የቬየትናምን ህዝብ የሚዋጉት ከሚልዮን ወታደሮች በላይ ናቸው።

በጀኔቫው ውል መሰረት በ1956እ.ም. ጠቅላላ ምርጫ መደረግ ነበረበት። ግን ያሜሪካን አሻንጉሊት የሆነው የዲየም መንግስት በሜሪካ መከሪት ምርጫው እንዳይደረግ ወሰነ። የቬየትናም ህዝብ የጀኔቫው ውል በሙላ መፍረሱን በግልፅ ተረዳው።የኢምፔሪያሊስቱ አሜሪካና አሻንጉሊቱ የሆነው የዲየም መንግስት ምርጫው እንዳይሆን ያደረጉበትን ምክንያት ለመረዳት ብዙም መድከም አያሻውም።በዚያን ጊዜ ያሜሪካን ፕሬዘዳንት የነበረው ጀኔራል አይዘንሃወር እንዳመነው፤በደቡብ ቬየትናም ምርጫ ቢደረግ ኖር የነፃነት ተዋጊዎቹ፤የሰሜኑ ፕሬዘዳንት ሆ ቺ ሚን ከመቶ ሰማኒያው በመረጠው ነበር፤ብሎ ተናገሯል።የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የዲየም መንግስት ምርጫው በመቅረቱ ተደስተው በሀገሩ ውስጥ ሀይላቸውንና ግዛታቸውን ለማደርጀት ቆርጠው ተነሱ።በህዝቡ ላይ የመረረ ስቃይ አደረሱበት።

ቀድሞ የፈረንሳይን ቅኝ አገዛዝ ሲዋጉ የነበሩት አርበኞችና ለመብታቸው ተቆርቋሪ የሆኑት ቬየትናሞች የውሉን መፍረስና የዲየምን መንግስት የጭቆና ተግባር ተመልክተው ከህዝቡ ጋር ስለፓለቲካና ብሄራዊ መብት በምስጢር መወያየት ጀመሩ። ይህ የሆነው ከ 1958 እ.ም. ጀምሮ ነው።

የዲየም መንግስት ግፈኛ ነበር።የገበሬውን ርስት ዘርፎ ለባላባቶች በመስጠት ልዩ ልዩ ህግጋት አውጥቶ የህዝቡን መብት በመግፈፍ፤ የቀድሞውን ተዋጊዎችና ባልደረቦቻቸውን በማሰር፤ ኢኮኖሚው እንዳይደረጅ አድርጎ ህዝቡን በማደህየት፤አገሪቱን የውጭ ሀይል እንዲጨቁናት አሳልፎ በመስጠቱ መላውን የቬየትናም ህዝብ አስመርሮት ነበር። በስር ቤት በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ሰዎች ያለ ፍርድ ያለ ጥፋት ታሰሩ፤ብዙ ሰዎች ደግሞ ያለሃጢአት ተገደሉ።

ከእስራትና ከሞት ያመለጡት ነፃነት ወዳዶች ከ1958እ.ም. ጀምሮ ባገራቸው የሰፈረውን የኢምፔሪያሊዝምና የጭቆና አስተዳደር ለመታወም ቁርጥ ሀሳብ አደረጉ።በየባላገሩና በየመንደሩ በድብቅ እየተዘዋወሩ ህዝቡን ማንቃቃት፤ማስተማርና አንዳንዱም የአድሀሪውን መንግስት የፖሊስና የወታደር ጣቢያዎች እየወጉ መሳሪያና የጦር ልምድ ማከማቸት ጀመሩ ።ያሻንጉሊቱ የዲየም መንግስት በጦር ሀይል እንጂ በሰላማዊ መንገድ የማይሻር መሆኑን ስለተረዱት፤ ሀይላቸውን ማዳበርና ተዋጊዎችን መመልመል ዋና አላማቸው ሆነ።ውጊያቸውና እንቅስቃሴያቸው በገጠር ነበር።ከ1958 እስከ 1960 እ.ም.ድረስ ተዋጊዎቹ እየበዙ፤እየበረቱና እየጠነከሩ ሄዱ። ይሁን እንጂ ቁጥራቸውና መሳሪያቸው

በአሜሪካን ከሚደገፈውና ከሚሰለጥነው የዲየም መንግስት ወታደሮች ጋር ሊወዳደር አይችልም ነበር። የያዙዋቸው መሳሪያዎች አብዛኞቹ ከዲየም ወታደሮችና ፖሊሶች የተወሰዱ ቢሆኑም ዘመናዊ አልነበሩም። ይህም ሆኖ ዲየምና የጦር ሀይሉ ሊገታቸው አልቻለም።

በ1960 እ.ም. ተዋጊዎቹ ውጊያውን የሚመራ አንድ አቀናባሪ በማቆም ሀይላቸውን አጎለመሱ። የደቡብ ቪየትናም የብሄራዊ የነጻነት ግንባር(የ.ብ.ነ.ግ) በየቦታው የሚገኙትን ልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጠቅልሎ ባንድ መስመርና ባንድ አላማ እንዲከሄዱ ለማድረግ ቻለ። ግንባሩ ቡዲስቶቹን፣ካቶሊኮችን፣ሪፐብሊካኖችን፣ሶሺያሊስቶችን፣ብሄራዊ አርበኞችንና ሀገር ወዳዶችን፣ትላልቅና ንኡስ ጉሳዎችን ባንድነት እንዲተሳሰሩ አደረገ። የውጭ እርዳታ ሳይጠይቅ በራሱ ሀይልና ጥረት ከመት ወደ አመት እያደገ፣ቀስ በቀስ የጠላቱን የዲየምን ሀይል እያደከመ መሄዱን አሜሪካኖች ከ1960 እ.ም. በኋላ ሊገምቱት ቻሉ።

የነጻነቱ ትግል እየተፋፋመ በመሄዱ ኢምፔሪያሊዝም መስጋት ጀመረ። በፊት በቪየትናም የአሜሪካን ወታደሮች ጥቂት ነበሩ፤ከ1960 እ.ም. በኋላ ግን በሽህና ባስር-ሽህ እየሆኑ መግባት ጀመሩ። የአሜሪካን ወታደሮች መጉረፍ ግንባሩን አላደከመውም። እንዲያውም ከራሱ ከአሜሪካ ወታደሮች ዘመናዊ መሳሪያዎች በመቀማት ሀይሉ እየበረታ ሄደ። ከ1960-1964 እ.ም. ድረስ የግንባሩ ተዋጊዎች በተዋጉ ቁጥር ድልን እያገኙ የዲየም ወታደሮች ደግሞ እየተሸነፉ ስለሄዱ አሜሪካን ቀስ በቀስ በቀጥታ ውጊያው ውስጥ መግባት ጀመረ። አያሌ የጦር ማቢያዎች ሰርቶ የወረራ ጦሩን አደረጀ።

በ1964እ.ም. አሜሪካን በቶንኪን ወደብ ላይ የሰሜን ቪየትናምን መርከቦች ተተናኩሉ ጥቂት መርከቦች ከሰመጠ በኋላ፤ ሰሜን ቪየትናም ያላንዳች ሰበብ ወግታናለች ብሎ የሀሰት ወሬ ነዝቶ በአይሮፕላን ሰሜኑን ወጋ። በ1965እ.ም. ሰሜን ቪየትናም ወደ ደቡብ ቪየትናም ጦር እየላከ የሳይጎኑን መንግስት ሊገለብጥ ይሻል የሚል መሰረት የሌለው ፕሮፓጋንዳ ነዝቶ ሰሜኑን በሰማይ መውረር ጀመረ። ከ1964እ.ም. በኋላ የአሜሪካን የወረራ ጦር እየተፋጠነ ግደግ ግድ ሆነበት። የባህር የአየርና የምድር ጦሩ በየወሩ ወደ ቪየትናም ይጉርፍ ጀመረ። በሀይል ብዛት የ

ነጻነት ተዋጊዎቹን አጠፋለሁ ብሎ ከግማሽ ሚልዮን የሚበልጥ ወታደርና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የፈጠራቸውን ልዩ ልዩ መሳሪያዎች ደረደረ። የሳይጎኑን መንግስት ወታደሮች ሞራላቸው ደክሞ፣ ቁጥራቸው መንምና መዋጋት ስላቃታቸው በ1967 እ. ም. አሜሪካ መላ ጦርነቱን እንዲዋጋ፣ ያሻንጉሊቱ የሳይጎን መንግስት ወታደሮች ሀጥታ ጠባቂ ዘበኞች እንዲሆኑ አደረገ። በ1968እ.ም. የአሜሪካ መንግስት ጦርነቱን ለማካሄድ ብቻ በወር ከ2ቢልዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ አውጥቷል። ግን ይህ ሁሉ ሆኖ ድል ማግኘት አልሆነለትም። በየጊዜው አደጋ መቀበሉ አልቀረለትም። በቅርቡ በመላው ቪየትናም የተደረገው፤አለምን ያስደነቀው የቴት በአል ውጊያና የግንባሩ ማጥቃት የአሜሪካንን ጀኔራሎች ከማስገረም አልፎ በፍፁም እንዲወናበዱ ታውቋል።

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጨካኝ አረመኔ ነው። በቅርቡ በአውሮፓ ተሰብስቦ የነበረው ኢንተርናሽናል የጦር-ወንጀል ችሎት (international warcrimes Tribunal) እንደፈረደው፤አሜሪካን በቪየትናም ህዝብ ላይ የህዝብ-መፍጀት-ወንጀል(genocide) ፈፅሞ ተገኝቷል።

አሜሪካ የቪየትናምን ህዝብ በብዙ አይነት ዘመናዊ መሳሪያዎች ፈጅቷል። ሲቪሉን፣ሽማግሌውን፣አሮጊቱን፣ህፃኑንና ሴቱን ያላንዳች ርህራሄ ግረዱ በይፉ ታውቋል። በመቶ-ሽህ የከተማና የመንደር ሲቪሎች ያላንዳች ጥፋት በቦምብ ተደብድበው ሞተዋል። ወደ ሁለት ሚልዮን የሚሆኑ ቪየትናሞች አረመኔው አሜሪካን እንደበረዶ ከሚያወርድባቸው ቦምብ ለመዳን ብለው፤ ወደ ትላልቅ ከተማዎች ሸሽተው ጥገኛ ሆነው፤የሚበሉትና የሚያርፉበት አጥተው ይሰቃያሉ። በናፓልም ቦምብ መርዝ ጢስና በበራሪ ቦምብ... የከተማውና የባላገሩ ህዝብ ተጨፍጭፏል። ናፓልም ከሰው ገላ ጋር እንደ ሙጫ ተጣብቆ ስጋን እያጠለ እሳቱ ሞት የሚያስጥ መሳሪያ ነው። የጀኔቫውን የጦር መሳሪያ ውል የጣሰው አሜሪካን በሁለት አይነት የመርዝ ጢስ ህዝቡን ያጠቃል። አንደኛው አይነት ሰውን አሰቃይቶ የሚገድል ነው፤ ሁለተኛው አይነት ደግሞ ሰብልን እህልንና ማንኛውንም አይነት ተክል የሚያጠፋ ነው። ከዚህ ግፍ በላይ አሜሪካ ትላልቅ የእስር-በረት ሰርቶ ፋሺስቱ ሂትለር ባየው ዘዴ መሰረት በሽህ የሚቆጠሩን መንደረተኞች ከቤታቸው በወ

ታደር ሀይል እያፈሰ፤ከርስታቸው እየነቀለና ከትውልድ ሀገራቸው እያባረረ በክረንቲ አጥር ውስጥ ከትቷል።

በሰሜንና በደቡብ ቪየትናም የቦምብ ዘረፋ በየቀኑ ይወርዳል።ራሱ የአሜሪካን መንግስት እንደተናገረው፤በሰሜን ቪየትናም ላይ የወረደው ቦምብ ብቻ በሁለተኛው የአለም ጦርነት በመላው አውሮፓ ከወረደው ይበልጣል።የአሜሪካ የአየር ሀይል የሰሜን ቪየትናምን ሞራል ለመስበር ብሎ ብዙ አይነት የአረመኔ ስራ ሰርቷል።ለጦር የሚያገለግሉን ነገሮች ነው የምደበድበው እያለ የሃሰት ወሬ በመንዛት የሰሜኑን ሲቪል ለመጨረስ ሞክሯል።ለጦር የሚያገለግሉ ነገሮች ማለት እንደ ጦር ፋብሪካዎች፤እንደ ድልድዮችና አውራ ጐዳናዎች፤እንደ የጦር ሰፈር ህንፃዎች ያሉና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው። እነዚህን ለማጥፋት የሚጣለው የቦምብ አይነት ከባድና ትልቅ ነው።አሜሪካን በሰሜን ቪየትናም የሚጠቀምባቸው የቦምብ አይነቶች ግን እንደዚህ አይነት አይደሉም።ሰውን የሚጨርሱ እንጂ ህንፃና ብረታ ብረት የማይጐዱ አይነት ናቸው።የፀሎት ቤቶችን፤ሆስፒታሎችን፤የህፃናት መሰብሰቢያዎችን፤ተማሪ ቤቶችን፤አደባባዮችን፤የርሻ ስፍራዎችን፤ገድቦችን፤ብዙ ህዝብ ያለባቸው ከተሞችንና እነዚህን የመሳሰሉትን ሲቪል የሚያዘወትራቸውን ስፍራዎች በአየር ቀጥቅጦ ብዙዎቹን ለማጥፋት ችሏል።አሜሪካ በቪየትናም ከኒውክሌር መሳሪያ በስተቀር ያልተጠቀመባቸው የጦር መሳሪያዎች የሉም።

ታዲያ ይህን ሁሉ ግፍ፤ይህን ሁሉ አሰቃቂ የአረመኔ ተግባር ፈፅሞ ያቀደውን ግብ ሊያገኝ ቻለን? በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በራሪዎች ተቃጥለውበታል።የአሜሪካን የጦር ፅህፈት ቤት ከ1961እ.ም. እስከ መጋቢት 1968እ.ም. ድረስ 24,000 ወታደሮች ሞተውብናል፤122,000 ቆስለውብናል ብሎ ተናግሯል።ፅህፈት ቤቱ የሰጠው ቁጥር ብ.ነ.ግ. ከሰጠው ቁጥር በጣም ያነሰ ቢሆንም አሜሪካ ሀይለኛ ቅጣት እንደተቀበለ ለመገመት የሚያስችል በቂ ምስክር ነው።አለም የአሜሪካንን መሸነፍ የተረዳው የቴት በአል ውጊያ ካለቀ በኋላ ነው። በቴት በአል መላው የቪየትናም ህዝብ ባንድ ላይ ተነስቶ ጠላቱ በየሰፈረበት ቦታ ገብቶ የጀግና ስራ ሰርቷል።ሰላሳ ያሜሪካን የአየር ሀይል ማቢያዎች ባንድ

ላይ ተጥቁ።ግንባሩ በሰጠው ቁጥር መሰረት አርባ-አምስት ሺህ የሳይጐን ወታደሮች አስር ሺህ የአሜሪካን ወታደሮች ጉዳት ደርሶባቸው ከጦርነቱ ውጭ ሆነዋል።አንድ ሺህ አምስት-መቶ በራሪዎች ተቃጥለዋል፤በሚልዮን ሊትር የሚቆጠር ነዳጅ አመድ ሆኗል።የጠላት ሀይል የሰፈረበት ቦታ አንድም ሳይቀር ተወርሮ ተቀጥቅጧል።የደቡብ ቪየትናም ከተማዎችና መንደሮች በመላ በግንባሩ ተይዘው ነበር።የግንባሩ ተዋጊዎች ሁዌ የሚባለውን ትልቅ የጠላት ጦር የሰፈረበትን ከተማ ነፃ አውጥተው ለሁለት ሳምንት ይዘውት ነበር።ግን አሜሪካ ለሲቪሉ ሳይራራ ከተማውን በመላ ስላቃጠለው ግንባሩ ከከተማው ለቆ ሄደ።ሳይጐን ከተማ ለሁለት ሳምንት ተሸብራ ነበር።የግንባሩ ተዋጊዎችና የሳይጐን ህዝብ ተነስተው ከተማውን ነፃ አውጥተው ነበር።ሌላው ቀርቶ በሀይል የተመሸገው የአሜሪካን ኤምባሲ ከወረራው ሊድን አልቻለም፤ ተዋጊዎቹ ኤምባሲው ውስጥ ድረስ ዘልቀው የህንፃውን ገሚስ አፍርሰው ሰራተኞቹን አሸብረዋል።ሮብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሳይጐን ወታደሮች ወደ ግንባሩ ዞረዋል፤በአስር ሺህ የሚቆጠሩ የጦር መሳሪያዎች ተማርከዋል፤ሃያ ሺህ የፖለቲካ እስረኞች ነፃ ተለቀዋል።በሳይጐን፤በሁዌና በሌሎች ከተሞች የወረዳ መንግስታት ተቋቁመው ስራቸውን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ።

አሜሪካ እየተሸነፈ የሄደ [illegible] ምንድነው?ህዝቡንና ብ.ነ.ግን ለመግረክ እንዴት አቃታቸው? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመርመር መጀመሪያ ሁለት ሀተታዎች መዘርዘር አለብን።

1ኛ. የአሜሪካና የቪየትናም ተዋጊዎች ጠቅላላ አላማ

2ኛ. የቪየትናም ጦረኞች የሚጠቀሙበት የውጊያ ስልት

3. የኢምፔሪያሊዝም አላማ፤የቪየትናም ህዝብ አላማ

ኢምፔሪያሊዝም በቪየትናም ያለውን አላማ ለመረዳት በጠቅላላው በአለም ላይ የወጠነውን ግብ ማወቅ ያሻናል።ድርሰቱ እንዳይራዘም ስለሌሎች የኢምፔሪያሊዝም እስረኞች ሳላወራ ስለቪየትናም ብቻ እተታለሁ።ይሁን እንጂ ኢምፔሪያሊዝም በቪየትናም ያለው ፖሊሲ (ኒሎች አገሮች ካለው ፖሊሲ ጋር የተያያዘ መሆኑን አንባቢው እ

ንዲገዙባልኝ ያሻል ።

ቬትናም ለአሜሪካ ምን ትጠቅማለች? የሚከተሉትን እንመልከት፡-

—ደቡብ ምስራቅ እስያ ብዙ የተፈጥሮ ሀብት አለው። አብዛኞች በዚህ ክፍለ- አለም የሚገኙት አገሮች የአሜሪካ የእጅ-አዙር ገዛቶች ናቸው።ሀብታቸው አሜሪካንን እንጂ ህዝባቸውን አያበለፅግም።ቬትናም በአሜሪካን እጅ ስላልገባችና ነፃ ለመውጣት እድል ስለነበራት ኢምፔሪያሊዝም ይህንን ለመቃወም ተነሳ።

—ነፃ ከወጣች ምሳሌ በመሆን በእስያ የሚገኙትን አሜሪካ በእጅ-አዙር የሚገዛቸውን ህዝቦች ታነቃቃለች።ለነፃነታቸው እንዲታገሉ ታደፋፍራለች።ኢምፔሪያሊዝም ይህንን ለመቃወም ተነሳ።

—ቬትናም ብዙ አይነት የተፈጥሮ ሀብት አላት።የእርሻና የማእድን ሀብቷ ከዚህ በፊት ፈረንሳይን ሲያበለፅግ ነበር ኢምፔሪያሊዝም ይህንን ሀብት ሊቀማ ተነሳ።

—የቬትናም ህዝብ ውጊያ የነፃነትና ሬቮሉሽናዊ ውጊያ ነው።የብሄራዊ የነፃነት እንቅስቃሴዎች ዛሬ የአሜሪካን እጅ-አዙር ገዛት በሆነው በ«ሶስተኛው አለም» ውስጥ እየበዙ በመሄዳቸው አሜሪካ ተጨንቋል።የቬትናም ህዝብ እንቅስቃሴ ከሁሉ የላቀ፤በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኘው ህዝባዊ ትግል ነው።አሜሪካ የቬትናምን ተዋጊዎች በማሸነፍ ሌሎቹ በፍርሀት ይጠፋሉ፤በማዛቴም «ሰላም» ይገባል ብሎ ያስባል።ቬትናም ነፃ ከወጣች ግን ሌሎቹ እንቅስቃሴዎች እርሷን አይተው ትግላቸውን ያፋፍሙታል የሚል ፕሮፓሬ አለው።ኢምፔሪያሊዝም ቬትናምን ድል አድርጎ «ቬትናምን እያያችሁ ተቀጡ» ብሎ የሌሎቹን ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ሞራል ለመስበር ታጥቋል።

—አሜሪካ«በሶስተኛው አለም»የተነሱትን እንቅስቃሴዎች ለማጥፋት ልዩ ልዩ ዘመናዊ መሳሪያዎች ፈጥሯል።የነፃ

ት ተዋጊዎችን የሚያጠቃ(Counter-insurgency) ዘመናዊ የሆነ ልዩ አይነት የጦር ሀይል አሰልጥኗል።እነዚህን መሳሪያዎችና የጦር ሀይል በቬትናም ለሞከርና በስራ ላይ አውሎ ውጤታቸውን ለመመርመር ይሻል።

—ቬትናም የህዝባዊት ቻይና ጐረቤት ናት።አሜሪካ ቻይናን የሚፈራት ስለ ጦር ሀይሏ ብቻ አይደለም። ቻይና የህዝባዊ ሬቮሉሽንን የምትደግፍና የምትረዳ ሀገር ናት። ሬቮሉሽናዊያን የሚያደንቋትና ከርሷም ትምህርትን ለማግኘት የሚፈልጓት ሀገር ነች።ዛሬ ብዙ ህዝባዊ ትግሎች ከህዝባዊት ቻይና በመማር ሬቮሉሽናዊ ትግል በየሀገራቸው ጀምረዋል፤ወደፊትም ይጀምራሉ። ኢምፔሪያሊዝም ቬትናምን አሸንፎጦሩን አስፍሮ ቻይናን ከእድገቷ ሊገታት ይሞክራል። ለብሄራዊ ተዋጊዎች የምትሰጠውን ሬቮሉሽናዊ ድጋፍ ሊከላከል ይጥራል።በህዝባዊት ቻይና ዙሪያ የጦር ማቢያዎች አቁሞ ሊተናኮላት ተነስቷል።

—ኢምፔሪያሊዝም ሬቮሉሽን በአለም ተሰራጭቶ፤የተጨቆነውና የተበዘበዘው ህዝብ ራሱን ነፃ አውጥቶ የመሻሻል ለውጥ እንዲመጣ አይፈልግም። ሬቮሉሽን በተነሳበት ሀገር ሁሉ እጁን ከቴር የለውጥ ተቃዋሚዎችንና ፀረ - ህዝብ የሆኑትን መደቦች በየጊዜው ይደግፋል።በቬትናም የያዘው ይሄንኑ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ከአሜሪካን አላማዎች ዋናዎቹ ናቸው።

የቬትናም ህዝብ የሚዋጋው ለምንድነው?

<u>የቬትናም ህዝብ የሚዋጋው ብሄራዊ ነፃነቱንና ህብረሰባዊ መብቱን ለማስከበር ነው።</u>

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የቬትናም ህዝብ አላማዎች የተለያዩ ስለሆኑ የሚዋጉትም በልዩ መንፈስ ነው።የአሜሪካን ወታደር የሚዋጋው ተገዶ ነው።ለሀገሩ፤ለርስቱ፤ለወገኑ የሚከላከል ስላልሆነ ሊሞት ሊቆስል አይፈልግም።ምንም እንኳ በመሳሪያ ቢያይልም አደጋ ያ

ለፀት ሕፍራ ውስጥ ለመግባት አይደፍርም። በጠቅላላው የደከመ ነው። የቬትናም ተዋጊ ግን በረቮሉሽናዊ መንፈስ ተመርቶ በድፍረትና በድ ፎ ይዋጋል። አንድ ቬትናማዊ ያለው ምርጫ መዋጋት ወይም በባርነ መኖር ስለሆነ ተዋጊ ለመሆን አያመነታም። ለሀገሩ፣ ለርስቱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለመ ብቱና ለነፃነቱ ሲል ሚከላከል ከአሜሪካን ወታደር የበለጠ ይደፍራል። ም ራሉ እጅግ የጠነከረ ነው። ኢምፔሪያሊዝም እንኳ የቬትናም ህዝብ ገያ፣ ሉዓላዊ አርባ አመት ቢሆንም፣ ሙሉ ነፃነቱን እስታገኝ ድረስ የሰፍ ጭ ትንግት ያሁሉ ሳያሽገሽግ ለመዋጋት ቆርጦ መነሳቱን አሳውቃል።

የቬትናም ተዋጊ አሜሪካንን የሚያህል ሀይለኛ ጠላት ሊ ያሸንፍ የቻለው መንፈስ ጠንካራ በመሆኑ ብቻ አይደለም። የሚጠቀ ሙበት የውጊያ ስልት ልዩ ስለሆነ ኢምፔሪያሊዝም ሊቋቋመው አልቻለም።

4 .የቬትናም ህዝብ የጦርነት ስልት

ጀኔራል ጂያፕ የቬትናም ህዝብ ፈረንሳይን እንዴት እሸነ ፈው ለሚለው ጥያቄ የቬትናም ህዝብ ፈረንሳይን ያሸነፈበት ዋና ም ክንያት የህዝባዊ ጦርነትን ደንብ ስለተከተለ ነው ብሉ ተናግሯል። ህዝባ ዊ ጦርነት(People's war) ማለት ምን ማለት ነው? በውጊያው ውስ ጥ መላው የተገለፀው ህዝብ ሲሳተፍ ህዝብ-አቀፍ ጦርነት ይባላል። ህዝብ አቀፍ ጦርነት ሁለት ተከታታይ ደንቦች ይዟል፤ አንደኛው፣ ውጊያው ረ ጅም ጊዜ የሚፈጅ መሆኑን ተዋጊዎቹ አውቀው እቅዳቸውን በዚሁ ሁ መሰረት ማቀናበር አለባቸው። ሁለተኛ፣ የውጊያው አይነት ድብቅ የአርበ ኞች ውጊያ(guerilla warfare) መሆን አለበት።

የቬትናም ጦርነት ህዝብ-አቀፍ ጦርነት ነው። ዋናዎቹ ተ ዋጊዎች ከህዝቡ ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ከህዝቡ የተለዩ አይደሉም። መላ ው የቬትናም ህዝብ ይደግፋቸዋል። ጠላት ሲመጣ ይደብቃቸዋል፤ ስለ ጠላቱ እቅድና ንቅናቄ ወሬ ያቀብላቸዋል። ምግብና ልብስ ገንዘብና ግ ሬሬያ ይሰጣቸዋል፤ ፖርተሮች ለሚያደርጉት መንቀሳቀሳቸውን ይቀበ ላል፤ ይደግፋል። ራሱን አደርጅቶ፣ ጠበንጃውን አንግቶ የሚያርሰው ገበሬ የብ. ነ. ግንባሩ ሲጠይቀው እርሻውን ትቶ ይዋጋል። ውጊያው ሲያበቃ

ወደ ስራው ይመለሳል። የአሜሪካን ወታደር ግንባር ለግንባር ተጋጥሞ የጠላቱን ቀበሌ መያዝ እንጂ የድ ብቅ፣ የሽምቅ ውርውርና የመዘዋወር ው ጊያ አያውቅም። ቬትናም ውስጥ የጦር ግንባር የለም፤ የጦር ግንባሩ መ ላው ሀገሩ ተዋጊው መላው ህዝብ ነው። የቬትናም ተዋጊ የሚዋጋው መንደርና ቀበሌ ለመያዝ ወይም ለመግረክ ሳያሆን ጠላቱን ለመደምሰስ ለመጉዳትና ለማድከም ነው። ጠላቱ ሊያጠቃው ሲመጣ ይሸሻል፤ ጠላቱ ሲያርፍ ባልታሰበ ጊዜ መጥቶ አደጋ ይጥልበታል፤ ወዲያውኑ ይሸሻል። ጠላቱ ካንድ ቦታ ወደ ሌላው ሲዘዋወር አድፍጦ በድንገት ይወጋውና ከመቅፅበት ዞር ይላል። የቬትናም ተዋጊ የትም ሊሄድ የትም ሊሰፍር ይችላል። የህዝብ ድጋፍ ስላለው በሄደበት ሁሉ ወዳጅ እንጂ ጠላት አ ያጋጥመውም።

የነፃነቱ ግንባር ውጊያውን በማካሄድ ብቻ አይወሰንም። በጉ ን ብዙ የማስተዳደር ተግባርችን ይፈፅማል። ተዘዋዋሪ ተማሪ ቤትሆስፒ ታል፣ የጋዜጣና የወሬ ማሰራጫ፣ የፖለቲካ ትምህርት መስጫ . . . እያቋቋ ሞ ህዝቡን ያገለግላል። የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና የገጠሩን ኢ ኮኖሚ ለማልማት ይታገላል። የህዝቡ የፖለቲካ መንፈስ ስለበሰለ ግንባ ሩ በሚተልማቸው የልማት ፕሮግራሞች ሁሉ በሙሉ ልብ ይሳተፋል።

የቬትናም ጦርነት ረቮሉሽናዊ ጦርነት ነው። የብ. ነ. ግ. ፕ ሮግራም የቬትናምን የፖለቲካና የኢኮኖሚ እጣም ለመለወጥ ስለሆነ ገበሬው፣ የእንዱስትሪ ሰራተኛውና የተማረው ሰው በሙሉ ተቀብሉታል የግንባሩ መሪዎች መሪ ለመሆን የቻሉት በትውልድ ወይም በሀብት ም ክንያት አይደለም። መሪዎቹ ከህዝቡ የፈለቁ ናቸው። የአስተዳደር ብልሹ ነት፣ አድሉትነት፣ ጉቦ መብላት፣ ህዝብ ማጥቃትና ማስመረር፣ የህዝብን ሀብት ለራስ ማድረግ . . . በብ. ነ. ግ. አስተዳደር ውስጥ ጨርሰው ጠፍተዋል።

የቬትናም ተዋጊ አሜሪካንን ሊያንቀጠቅጥ የቻለው ከላ ይ በተጠቀሱት ምክንያቶችና የሞራል ብልጫ ስላለው ነው። ለነፃነቱ የ ሚዋጋ ሁሉ በህዝብ-አቀፍ ጦርነት ከተቋቋመ ድል እንደሚያደርግ አ ይጠረጠርም። የቻይናን፣ የኩባ፣ የቬትናም(ከ1954 በፊት)የአልጀሪያ ህዝ ብ ህዝብ-አቀፍ ጦርነት አድርጎ ነፃነቱን እንዳስከበረ ታሪክ ይመሰክራ ል። ዛሬ የቬትናም የብሄራዊ የነፃነት ግንባር ጠላቱን ኢምፔሪያሊዝም

ን እያሸነፈ መሄዱ ይታያል።

እኛ የኢትዮጵያ ሬቮሉሽናዊያኖች ከዚህ ምን ትምህርት እናገኛለን?

5. የቪየትናም ጦርነትና የእኛ ትግል

ከሁሉ አስቀድሞ ሬቮሉሽናዊ ትግል ምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል።ሬቮሉሽናዊ ትግል የሕዝብ ትግል ነው።ሬቮሉሽን የአንድን አገር ጠቅላላ አቋም ለመለወጥ የሚደረግ ትግል ስለሆነ መላው ሕዝብ መሳተፍ አለበት።መላው የቪየትናም ሕዝብ ለትግሉ ህይወቱን ሊሰጥ ስለቆረጠ ኢምፔሪያሊዝምን ለማጥቃት ቻለ።

ሁለተኛ፤ሕዝቡ በትግሉ ውስጥ እንዲገባ የፖለቲካ መንፈሱ መጉልመስ አለበት ጠቅላላው አስተያየቱ ተለውጦ የሚደርስበት ግፍና ጭቆና እግዚአብሄር የደነገገው ሳይሆን የሚገዙት ሰዎች የሰሩት መሆኑን በግልፅ ማወቅ አለበት።የቪየትናም በፖለቲካ የላቀ ነው፤ጠላቱን ና ወዳጁን የለየ ነው፤የትኑርውን ማሻሻያ ዘዴ አጥብቆ ያውቃል።እኛም የሀገራችንን ሰርቶ አደር ሕዝብ ፖለቲካ አስተያየት እንዲዳብር መልፋት አለብን። ሕዝቡ የኢምፔሪያሊዝምን ውስጠ-ምስጢር መገንዘብ አለበት።ትግሉ ሲፋፋም ትጥቃችን ሲደረጅ ኢምፔሪያሊዝም ጨቋኙን መንግስት ረድቶ ሕዝባችንን በግፍ ሊፈጅ እንደሚነሳ በግልፅ አውቀን ለሰፊው ሕዝብ ማስረዳት ያሻናል፤ግልፅ የሆነ የፖለቲካና የሬቮሉሽናዊ ፕሮግራም በየጊዜው እያወጣን ሕዝቡ እንዲያጠናው እንዲያሻሽለው ለሕዝቡ ማቅረብ አለብን።ከሕዝቡ ጋር በጥብቅ መተሳሰርና የጠነከረ ህብረት ማቆም አለብን።

ሶስተኛ፤ውጊያውን የሚጀምረው የመሰረታዊ ለውጥን ትርጉም አጥብቆ የተረዳውና ጠላቱን ከወዳጁ የለየው፤በብሄራዊ ስሜት የነደደውና በሀገር ፍቅር የተሞላው፤ዘረፋንና ብዝበዛን ለማጥፋት የሚሻው፤የፖለቲካ አመራር ችሎታ ያለው ግንባር-ቀደም ድርጅት ነው፤ይሁን እንጂ እኔ ትእዛዝ ሰጪ ነኝ ሕዝቡ አይኑን ጨፍኖ ይከተለኝ አይልም።ሕዝቡና ግንባሩ አንድ ናቸው።ግንባሩ ከሕዝብ ከተለየ፤የሕዝብ ድጋፍ ከሌለው የብሄራዊ ጠላቱን ሊደመስስ እንደማይችል ያውቃል። ሕዝቡም ይህንን ያውቃል።አላማችን ዲሞክራሲያዊ የሆነ ድርጅት አቋመን ድርጅቱ ከሕዝብ ጋር እንዲጣበቅ ማድረግ ነው።

አራተኛ፤የኢትዮጵያ ሬቮሊሽናዊያን ሕዝቡን ማክበር አለባቸው።በሕዝብ ላይ ትልቅ እምነት ሊኖራቸው ያስፈልጋል።ሕዝቡ ካልተነሳ በሀገራችን ያለው በኢምፔሪያሊስቶች -በተለይ በአሜሪካን- የሚደገፈው የግፍ አገዛዝ ሊሻር አይቻልም።ተዋጊውና መሪው ሕዝቡ መሆን አለበት።

ሕዝብ ስንል ምን ማለታችን ነው? ሁለት መሰረታዊ ልዩነቶችን ማድረግ አለብን፤የሕዝብ ጠላት ወይንስ የሕዝብ ወገን።የሕዝብ ጠላት የሆኑት ንጉሱ፤መኳንንቶች፤መሳፍንቶች፤ታላላቅ ባላባቶች፤ ታላላቅ የቤተ ክህነት አለቆች፤አድር-ባዮችና አድሀሪውን አቋም ደጋፊዎች በሙሉ ናቸው።እነዚህን ፀረ-ሬቮሉሽናዊ ብለን እንሰይማቸዋለን። ሕዝብና የሕዝብ ወገን ብለን የምንጠራቸው፤የእንዱስትሪ ሰራተኛ መደብንና አርሶ-አደሩን ገበሬ፤በየከተማው ያለውን ድሀና ስራ የተነፈገውን ሕዝባዊ ክፍል፤የብሄራዊ ስሜት ያላቸውን የተማሩ ሰዎችና ለውጥ ፈላጊዎችን በሙላ ነው።

እንግዲህ በሀገራችን የሚነሳው ትግል በመጀመሪያው ክፍልና በሁለተኛው ክፍል በተጠቀሱት መደቦች መሀከል ነው።በመጀመሪያ የተጠቀሰው መደብ ጨርሶ የለውጥ ተቃራኒ ነው።የሚመራው የመደብ ጥቅሙን በመመልከት ብቻ ነው። ቀጥለን የተመለከትነው ሕዝባዊ ክፍል ግን ለውጥን ይፈልጋል።ከመጀመሪያው መደብ ጭቆና፤ዘረፋና ብዝበዛ ራሱን ነፃ ለማውጣት ይፈልጋል።ሆኖም በዚህ ውስጥ ያሉት ህይሎች የተለያዩ ንኡስ አላማዎች ይኖሯቸዋል። ግንባር-ቀደሙ ድርጅት እነዚህን አላማዎች ከትግሉ እድገትና ደረጃ ጋር እያስተያየ ማዋሀድና ማቀናበር አለበት ። የኢትዮጵያ ሬቮሉሽናዊ ሕዝቡ ራሱ ትግሉን ለማካሄድ፤ለመምራትና በመጨረሻም ድልን አግኝቶ ራሱን ለማስተዳደር እንደሚችል በትክክል መገንዘብ አለበት።ሕዝቡ እንዳሽከር የሚከተል ሳይሆን የለውጥ ሀይልና አላማ ነው።

አምስተኛ፤የትግሉ አላማ ለሕዝብ ጥቅም የሚውል መሆን አለበት።የቪየትናም ትግል ግቡ ብሄራዊ ነፃነት ለማግኘት፤ትክክለኛ ፍርድ ለመመስረት፤ጭቆናን ለማጥፋት ነው።የሀገር ሀብት የሕዝቡ እንጂ የጥቂት በዝባዦች መሆኑ እንዲቀር፤ትክክለኛ የርስት ድልድል እንዲ

ምንዝንር መቻቻልና የኢኮኖሚ እድገት እንዲመጣ ነው። ይህ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚለማመደውና የሚደገፈው ነው። የትግሉ አላማ ለህዝብ ጥቅም ካልሆነ ህዝብ አይከተለውም። ያለ ህዝብ ድጋፍ ፈሽስትን ለማድረግ አይቻልም።

እድገትኛ የፊውዳሊዝም ትግላችን ረጅም ጊዜ የሚፈጅ መሆኑን አስቀድመን መገንዘብ አለብን። የመሳሪያችን እድገት ህዝብ-አቀፍ መሆን አለበት። በአለማችን መንገድ የኢትዮጵያን አቋም ለመለወጥ ከአለተቻለ ከአመቻቸት በሚገኙት ጋር ወር ለማንሳት ግፈግፈን የለብንም ያለእንዳች ርህራሄ በህዝቡ ላይ የሚፈጸመውን ግፍ ለማስወገድ ወር ለማንሳት መልፋት አለብን። የመጨረሻው ድል የህዝብ ነው።

ትግላችን በህዝብ ተደገፎ ከህዝብ በሚያገኘው ሀይል ና ጥረት ብቻ መከድ አለብት። ለትግላችን ብቸ ፍሬ ሊያስገኝለት እንደሚችል ማወቅ ያስፈልገናል። የህገሬችን ገጠሮች በኢምፔሪያሊስቶች-በተለይ በአሜሪካን-መደገፉቸውን ብናውቅም እኛ የውጭ ሀይል ይረዳና ል ብለን አቀኞችን በዚህ መልኩ ማውጣት የለብንም። የተገኙ ጥቋቻችን እምነት በኢምፔሪያሊስቶች-በተለይ በአሜሪካን-ላይ ነው። የኛ ድጋፍ በሰፊው ህዝብ ላይ ነው። ይህ መሬታዊ ለፍላታችን ነው።

ከኢትዮጵያ ወርነት ከላይ የተጠቀቁትንና እነርሱን የመሰሉ ፍሬ ነገሮች ለናገኝበት እንችላለን። ይህንንም ስለ በኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም ውስጥ የፈለቁትን ዘዴዎችና ፕሮግራሞች በተጥታ ገለፃልን ለትግላችን እናውላቸው ግልፅ አይደለም። ከኢትዮጵያ የምናገኘውን ትምህርት ለህገሬችንና ለትግላችን ተስማሚውን ፈልቅቀን ማድቀቅ የኛ ፈንታ ነው። ከአቀድመን ግን የህገሬችንን ሁኔታ መመርመር እለብን። ተመርምሮ ሁኔታው በደንብ ሲታወቅ ከኢትዮጵያ ትግል መሬ የሆኑትን ዘዴዎች ወለደን የኢትዮጵያን ምሳሌ መከተል አለብን። ኢትዮጵያ እንደጥበብን ፋና ነችልኢርቢን መከተል ፊውዳሊዝምና ግዴታችን ነው።